# የእግዚአብሄር መገኘት ድላችን ነው

ጃኪይ ኦስክ

የእግዚአብሄር ህዝብ የተስፋይቱን ምድር መውረሳቸው እና በዚያም መኖር መጀመራቸው በእግዚአብሄር ዘንድ ምን ሊፈጥር እንደሚችል ታሪኩን ከመፅሐፈ ኢያሱ እና መፅሐፈ ከመፅሐፈ መመልከት

" .........ቃልህን በልቤ ሰወርኩ..........."

መዝሙር 119፡74

ትምህርት አንድ

1. ለአዲሱ የእስራኤል መሪ የእግዚአብሄር መመሪያ
2. ገለፃ እና ትግበራ
3. ሁለቱ ሰላዮች በተልእኮ ላይ
4. የቃልኪዳኑ ታቦት ሚና
5. እስራኤል እንደ ማህበር

ትምህርት ሁለት

1. ቃልኪዳን ፣ግርዛት፣እና ማህበር
2. ኢያሪኮን መዞር
3. የእስራኤል ድል
4. የእስራኤል ሽንፈት
5. የኃጢአት ውጤት

ትምህርት ሶስት

1. ገለፃ፣ትግበራ ፣እና ማሰላሰል
2. ለመውረስ የተደረገ ውጊያ
3. ምድሪቱን ማፅዳት
4. ምድሪቱን ለሁሉም እንደየድርሻው ማከፋፈል
5. የኢያሱ ስንብት

ትምህርት አራት

1. ጥሪ ለተሰጠ ህይወት
2. እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ሳያጠፉ ቀሩ
3. እግዚአብሄር መሳፍንትን አስነሳ
4. የእስራኤል የባህሪ ይዘት
5. አስታውሱ

ትምህርት አምስት

1. እግዚአብሄር ቃልኪዳኑን አሰበ
2. ናዝራዊው ሶምሶን
3. የሶምሶን ባህሪይ መገለጥ
4. በሶምሶን ጥንካሬ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተገለጠ
5. ልክ የሌለው የበቀል ፍላጎት

ትምህርት ስድስት

1. ዳኛው እግዚአብሄር ነው
2. በቀል የእግዚአብሄር ነው
3. ሶምሶን እና ደሊላ
4. የሶምሶን እና የእኛ ባህሪይ
5. የሶምሶን አይን መጥፋት

## መቅድም

ይህንን *"የእግዚአብሄር መገኘት ድላችን ነው"* የሚለውን ክፍል እያጠናችሁ እያለ ትምህርቱ ቀሪውን የህይወት ዘመናችሁን ቅርፅ እንዲያስይዝ ተደርጎ እንደተሰራ ታስተውላላችሁ፡፡ በዚህ ልዩ የሆነ የጥናት ጉዞ ተጠቃሚነታችሁ ለጥናቱ ባላችሁ መስጠት እና ብርቱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ ይህን ጥናት በሙሉ ልባችሁ ማጥናታችሁ እግዚአብሄር በቃሉ በኩል ለሰው ልጆች የሰጠው የበረከት ቃል ኪዳን በህይወታችሁ እንዲገለጥ ያደርገዋል፡፡

ይህን ክፍል ስታጠኑ እንደ ከዚህ በፊቱ ሁሉ በእጃችሁ ሊኖሯችሁ የሚገቡትን የጥናት መርጃ መሳሪያዎች መያዝ አትዘንጉ፡፡እነዚህም መሳሪያዎች ሁል ጊዜ ስታጠኑ ሊኖሩአችሁ ይገባል፡፡በየእለቱ በሚኖራችሁ የጥናት ፕሮግራሞች ላይ ሁሉ መያዝ ይኖርባችኋል፡፡

1. *"የእግዚአብሄር መገኘት ድላችን ነው"* የሚለውን የጥናት ክፍል ጥራዝ
2. አዲሱ መደበኛ ትርጉም መፅሐፍ ቅዱስ ፡፡የምትገዙት አዲስ መፅሐፍ ቅዱስ ከሆነ የሚከተሉትን ነገሮች ያካተተ ቢሆን ይመረጣል፡፡
   ሀ. እያንዳንዱ የመፅሐፍ ቅዱስ መፅሐፍት ስም ማውጫ ያለበት
   ለ. በመፅሐፉ ገፅ ላይ ባሉ ቁልቁል በተፃፉት ሁለት ረድፎች መካከል ያሉ ማጣቀሻዎችን የያዘ
   ሐ. ጥቅስ ማውጫ በጀርባው ላይ ያለው
   መ. መሰረታዊ የሆኑ ካርታዎችን የያዘ ቢሆን ይመረጣል
3. እስኪብርቶ ወይንም እርሳስ እንዲሁም ምልክት ማድረጊያ የተለያየ ከለር ያለቸው ማርከሮች
4. ማስታወሻ ደብተር ወይንም ሌሎች ማስታወሻ የመያዣ ቁሶች ለምሳሌ ሞባይል መሰል ማስታወሻ መያዣዎችን(ታብሌቶችን) መጠቀም ትችላላችሁ
5. 3 በ 5 ወይንም 4 በ 8 የሆኑ ካርዶች

*መፅሐፍ ቅዱሳችሁ በተራ ቁጥር ሁለት ላይ ያሉትን 4 ነገሮች ያካተተ ከሆነ ጥናታችሁን በተሳካ መልኩ ማከናወን እንድትችሉ ይረዳችኋል፡፡መፅሐፍ ቅዱስ ስትገዙ በመፅሐፍ መሸጫ መደብር ውስጥ ያሉ የሽያጭ ሰራተኞች እንዲረዷችሁ መጠየቅ አትፍሩ፡፡በተለይ በአግባቡ የተቀመጠ ማጣቀሻ ያለባቸውን መፅሐፍት ለመግዛት የሽያጭ ሰራተኞችን ብትጠይቁ መልካም ነው፡፡*

*ሌላው ማወቅ ያለባችሁ ፡ በዚህ ግዜ የተለያዩ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በአማርኛ ቋንቋ ይኖራሉ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ የመፅሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችን በመፅሐፍት መደብሮች ውስጥ ታገኛለችሁ፡፡በተለይ ጥናታችሁን በአግባቡ ለማከናወን ከሚረዷችሁ የትርጉም አይነቶች አንደኛው ማብራሪያ ያለው አዲሱ የአማርኛ መደበኛ ትርጉም መፅሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ይህ የሆነበት ምክንያት አተረጓጎሙ ቀላል እና በዘመናዊ በሆነ የአማርኛ ቋንቋ መሆኑ ነው፡፡ስለዚህ ይህንን የትርጉም አይነት መጠቀም በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን ሀሳብ በቀላሉ እንድትረዱ የግዛችኋል፡፡ይህ መፅሐፍ  ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ሰዎች ታስቦ ነው የተዘጋጀው፡፡ተጨማሪ ማብራሪያዎችን የያዘ በመሆኑ ብዙ ልትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡*

*በመፅሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ለመፃፍ እና ማስታወሻ ለመያዝ ብዙ አይክበዳችሁ ምክንያቱም እርሳስ ፣እስኪብርቶ እንዲሁም ምልክት ማድረጊያ ማርከሮች እንዲኖራችሁ የተፈለገው በዚህ መልኩ እንድትጠቀሙባቸው ነው፡፡ልታጠኑት የገዛችሁት የራሳችሁ መፅሐፍ በመሆኑ አክብቡበት ፣የቀስት ምልክት እንዲሁም የተለያዩ ምልክቶችን አድርጉበት፡፡ከዚህ በተጨማሪም ማስታወሻ ደብተራችሁን ፣ሞባይላችሁን፣የድምፅ መቅጃ መሳሪያዎቻችሁን በጥናታችሁ ውስጥ የተለያዩ ሃሳቦችን ፣ጥያቄዎችን ለመያዝ እንድትችሉ ይረዷችኋል፡፡*

*እያንዳንዳቸው በአምስት ክፍሎች የተከፋፈሉ ስድስቱም የጥናት ክፍሎች  በዚህ ጥናት ውስጥ ተካተዋል፡፡ይህ የሆነበት ምክንያት እነዚህን ጥናቶች በግዜ ከፋፍላችሁ ማጥናት ትችሉ ዘንድ ነው ፡፡በአንድ ግዜ ቁጭ ብላችሁ አንዱን ክፍል ልታጠኑት ወይንም ደግሞ ተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቃችሁ ይችላል በመሆኑም ለእናንተ አመቺ በሆነ ሁኔታ ልታጠኑት ትችላላችሁ፡፡*

*መፅሐፍ ቅዱስን ስታጠኑ የመጀመሪያችሁ ከሆነ ከዚህ ክፍል አስቀድማችሁ “መፅሐፍ ቅዱስን የራስ ማድረግ” የሚለውን የጥናት ክፍል በቅድሚያ እንድታጠኑት እመክራችኋለሁ፡፡*

ይህ የጥናት ክፍል የተዘጋጀው መፅሐፍ ቅዱስን እንዴት ማጥናት እደሚቻል ለማሳየት ታስቦ በመሆኑ ይህንን ክፍል ቀድሞ ማጥናት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

- የዘፍጥረትን መፅሐፍ የመጀመሪያዎቹን አስራ አንድ ምዕራፎችን የያዘውን *"የእግዚብሄር እቅድ እና የእኛ ምርጫ"* የሚለውን የጥናት ክፍል ፡፡
- ከዘፍጥረት 12-25 ያለውን *"የእግዚአብሄር ተስፋ እና በረከታችን"* የሚለውን ክፍል፡፡
- ከዘፍጥረት 25-36 ያለውን *"የእግዚአብሄር ታማኝነት እና ተስፋችን"* የሚለውን ክፍል
- ከዘፍጥረት 37-50 ያለውን *"ነፃነታችን የሆነው የእግዚአብሄር ይቅርታ"* የሚለውን ክፍል፡፡
- *"ነፃ ያወጣን የእግዚአብሄር ጥሪ"* ክፍል አንድ እና ክፍል ሁለት በተጨማሪም የዘፀአትን መፅሐፍ የያዘውን የጥናት ክፍል ፡፡

እነዚህን ጥናቶች እንድታጠኗቸው ብናበረታታችሁም ሁሉም ጥናቶች እራሳቸውን ችለው የተዘጋጁ ስለሆኑ *"ድላችን የእግዚአብሄር ህልውና"* የሚለውን ክፍል እንድታጠኑ የሚያግዧችሁ ነገር የለም፡፡ በመጨረሻም እንድትረዱት የምንፈልገው ይህ ጥናት በግላችሁ ያለምንም አስተማሪ በቀላሉ እንድታጠኑት ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ነው፡፡ ፕሮግራም አውጥታችሁ በአግባቡ ካጠናችሁት ያለምንም ችግር ልታጠናቅቁት ትችላላችሁ ጥናቱም በጣም አስደሳች ይሆንላችኋል፡፡ብዙ አዳዲስ መረጃዎችን ታገኙበታላችሁ ያገኛችሁትንም ትምህርት እና መረዳት ከሌሎች ጋር እንድትካፈሉት ፍላጎት ያሳድርባችኋል፡፡ ይህን ክፍል ስታጠኑ መልስ የሚሹ አንዳንድ አስቸጋሪ ጥያቄዎች ሊገጥሟችሁ ይችላል፡፡

ሰዎችን ወደዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት መጋበዝ ትችላላችሁ፡፡ምናልባትም ከእጮኛችሁ ጋር በመሆን እንደ እናንተ የሆኑ ሁለት ወይንም ሶስት ጥንዶችን ወደዚህ ጥናት መጋበዝ ትችላላችሁ፣ ወይንም ደግሞ የምትኖሩት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ከሆነ በዚያ የተዋወቃችኋቸውን ሰዎች መጋበዝ ትችላላችሁ ወይንም ደግሞ በስራ ቦታዎቻችሁ የምትተዋወቋቸውን የስራ ባልደረቦቻችሁን እስቲ እግዚአብሄር በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን እንደተናገረ አብረን እናጥና ብላችሁ ወደዚህ ጥናት መጋበዝ ትችላላችሁ፡፡ምናልባትም በሳምንት ውስጥ ምን እንደተማሩ ተገናኝተው ስለመፅሐፍ ቅዱስ የመወያየት ልምድ ያላቸው ሰዎች

ያሉበት ቤተክርስቲያን አባል ትሆናላችሁ ወይንም ደግሞ እንደዚያ አይነት ሰዎች ታውቁ ይሆናል አነሱንም ጋብዟቸው፡፡በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ መፅሐፍ ቅዱስን በጋራ ተሰብስባችሁ ልታጠኑ እና መረዳታችሁን ልትከፋፈሉ የምትችሉበትን ጤናማ ሁኔታ ለመፍጠር ሞክሩ፡፡እርስ በእርሳችሁ ስታጠኑ እናንተ መረዳታችሁን ለሌሎች ስታካፍሉ እናንተም ከሌሎች ስትካፈሉ አብራችሁ ማደግ ይሆንላችኋል፡፡

አሁን ጥናታችንን የምንጀምርበት ጊዜ ነው! መፅሐፍ ቅዱሳችሁን መፅሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 1 ላይ ክፈቱ አስገራሚውንም ጉዞ ቀጥሉ፡፡

**መግቢያ**

እስራኤላውያን የተስፋይቱ ምድር መግቢያ ላይ ደርሰዋል፡፡ጉዞው ረጅም እና አስቸጋሪ ነበር፡፡ብዙ ቤተሰቦች እና ጓደኞቻቸው በመንገድ ላይ ሞተዋል፡፡አሁን ስለቀደሙት አባቶች ምንም እውቀት የሌለው አዲስ ትውልድ ተወልዷል፡፡ይህ ትውልድ ከፈርኦን ምግብ ለመግዛት ወደ ግብፅ በተደረገው ጉዞ ላይ አልተሳተፈም፣ ወይንም ደግሞ የግብፃውያን በኩሮችን በመቅሰፍት ሲመታ አልነበረም፡፡ እስራኤልም ከግብፅ እንዴት እንደወጣ አላዩም ነገር ግን ወደ አባቶቻቸው ምድር ገቡ፡፡

አንድ የሚያውቁት መሪ ሙሴ ነበር እሱም ሞቷል፡፡አሁን ሙሴ በኢያሱ ተተክቷል ነገር ግን ዮርዳኖስን አቋርጦ ለአብርሀም ተስፋ ወደሰጠው ምድር ለመግባት ከእግዚአብሄር ትእዛዝ እየጠበቀ ነው፡፡ብዙ አመታት አልፈዋል፡፡ብዙ አዳዲስ ሰዎች ተወልደዋል ብዙዎች ደግሞ ሞተዋል፡፡ታላላቅ መሪዎች አርጅተው ሞተዋል አዳዲሶች ተተክተዋል፡፡ነገር ግን በዚህ ሁሉ ዘመን ሰዎች ይለዋወጡ እንጂ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር ፈፅሞ አልተለወጠም፡፡ህዝቡን ከግብፅ ባርነት ነፃ አውጥቶ ወተት እና ማር የምታፈሰውን ምድር ለማውረስ የገባውን ተስፋ አልዘነጋውም፡፡

ይህ *"ድላችን የእግዚአብሄር ህልውና"* የሚለው የጥናት ክፍል እስራኤላውያን እንዲወርሱ የተሰጣቸውን ምድር እንዲወርሱ ያስቻሏቸውን አንዳንድ ሰዎችን እና ክስተቶችን ያስተዋውቀናል፡፡ በተጨማሪም ደግም እስራኤላውያን የተሰጣቸውን ምድር ሙሉ በሙሉ መውረስ አለመቻላቸው እና አለመታዘዛቸው ያስከተለባቸውን ውጤት ገልጦ ያሳየና፡፡ ከነአናውያን፣ኬጢያውያን፣አሞራውያን፣ባጠቃላይ በዚህ ክፍል የተዘረዘሩ ሁሉም "ውያን"

ከምድራቱ መወገድ አለባቸው፡፡እስራኤላውያን ይህንን ትእዛዝ መታዘዝ ባለመቻላቸው ምክንያት ሌሎች አማልክቶችን ፣ከእንጨት እና ከድንጋይ የተሰሩ ጣኦታትን የማምለክ ባህል ቅዱስ ወደሆነው የእግዚብሄር ህዝብ መካከል እንዲገባ አደረገ፡፡የመሳፍንት መፅሐፍ ይህንን ክፉ የሆነ የእስራኤል የታሪክ ወቅት ምስል ያስቀምጥልናል፡፡

በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ የተላለፉት መልእክቶች ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ነዋሪዎች ብዙ ተግዳሮቶች አሏቸው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ ለህይወታችሁ ብርታት እና ጥንካሬ የሚሰጡ ትምህርቶች ታገኙባቸዋላችሁ፡፡እንደዚህ ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ፡ እነዚህ ከብዙ ሺህ አመታት በፊት የተፈፀሙ ታሪኮች በዚህ ዘመን ለምንኖር ሰዎች ምን አይነት ጠቀሜታ ሊኖራቸው ይችላል? የእግዚአብሄር መንፈስ በኃይል እንዲሰራ እራሳችሁን ክፍት አድርጋችሁ ተጠባበቁ፡፡በቃሉ ውስጥ ለህይወታችሁ የሚተላለፈውን መልእክት ልባችሁን ክፍት አድርጋችሁ በእምነት ተቀበሉ፣ እርሱም እንደማይጥላችሁ፣ እንደማይተዋችሁ እንደዚሁም ህልውናው ከእናንተ ጋር በመሆኑ ምክንያት በህይወታችሁ ውስጥ ለሚገጥማችሁ ውጊያ እና ተግዳሮት እንዳትፈሩ ድልን እንደሚሰጣችሁ በህይወታችሁ ሁልጊዜ ማሸነፍን የምታገኙት በእርሱ እና በእርሱ ብቻ እንደሆነ ማመን አለባችሁ፡፡

## ትምህርት አንድ -  ክፍል 1

**መግቢያ:**

አዲሱ የእስራኤል መሪ ኢያሱ ነው፡፡ሙሴ ለአርባ አመታት ያክል ህዝቡን በምድረበዳ መርቶአል፡፡አሁን ደግሞ የሙሴ ረዳት የሆነው ኢያሱ ይህን ብዙ ህዝብ እግዚአብሄር ለአባቶቻቸው ቃል ወደገባላቸው ምድር ለማስገባት ሙሉ ስልጣኑን እና ሃላፊነቱን ተረክቧል፡፡እግዚአብሄር ከብዙ መቶ አመታት በፊት የገባላቸው ተስፋ አሁን አብርሀምን፣ይስሀቅን እንዲሁም ያዕቆብን ለዘነጋው ትውልድ እውን ሊሆን ነው፡፡እነዚህ አባቶች እግዚአብሄር የገባላቸውን የተስፋ ቃል በእምነት ተቀበሉ ይህ ትውልድ ግን የተስፋውን ፍፃሜ በአካል ወረሰ፡፡

ለብዙ አመታት በምድረበዳ ከመንከራተት በኂላ በመጨረሻ የተስፋይቱ ምድር መግቢያ ላይ ደረሱ፡፡ዮርዳኖስን ተሻግረው በኬጢያውያን፣በከነአናውያን፣በአሞራውያን፣በፌርዛውያን እንዲሁም በኢያቡሳውያን ነገስታት ተይዛ ያለችውን የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ ቸኩለዋል፡፡በእርግጥ ይህቺን ምድር ለመውረስ ጦርነት ይካሄዳል ፣ደም ይፈሳል ህይወት ይጠፋል፤ ነገር ግን ነገስታቶቹ ሁሉ ድል ተነስተው ድሉ የእስራኤል መሆኑ አይቀርም፡፡

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 1 አንብቡ ፡እነዚህን አራት ነጥቦች በጥንቃቄ ተመልከቱአቸው፡፡

- የምድሪቱ ድንበር
- እግዚአብሄር ለኢያሱ የሰጠው ተስፋ
- የማበረታቻ ቃል በዚህ ምዕራፍ ተደግሟል
- የህዝቡ ምላሽ ለኢያሱ ትእዛዝ

**መልመጃ:**

ምን ተመለከታችሁ?

1. በቁጥር አራት መሰረት የትኛው ድንበር ነው ምድሪቱን የሚገልፀው?

ሀ. በደቡብ በኩል_______________________________________________

ለ. በሰሜን በኩል_______________________________________________

ሐ. በምስራቅ በኩል_____________________________________________

መ.በምዕራብ በኩል_____________________________________________

2. በቁጥር 5 መሰረት እግዚአብሄር ለኢያሱ የገባለት ተስፋ ምንድነው?

ሀ._________________________________________________________

ለ._________________________________________________________

ጥያቄ፡ ለምንድነው ኢያሱን ማንም ሊቋቋመው ያልቻለው? እስራኤላውያን ቁጥራቸው ብዙ ስለሆነ ይሆን? ጠንካሮች ስለሆኑ ይሆን? ወይንስ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ስለታጠቁ ይሆን? መልሱ ያለው በእግዚአብሄር ተስፋ ውስጥ ነው፡፡ ለመሆኑ እግዚአብሄር የገባላቸው ተስፋ ምን የሚል ነበር?

_________________________________________________________

_________________________________________________________

3. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለአራት ጊዜ ያክል ተደጋግሞ የተጠቀሰው ቃል ምን የሚለው ነው?

_________________________________________________________

_________________________________________________________

ባለ ከለር እርሳሶቻችሁን በመጠቀም እነዚህን ቃላቶች ምልክት አድርጉባቸው፡፡

ሀ. ለምንድነው እግዚአብሄር እነዚህን ቃላቶች በቁጥር 6 ላይ የተጠቀመው ?

_________________________________________________________

_________________________________________________________

ለ. እንደገና በድጋሚ በቁጥር 7 ላይ ተጠቅሚቸዋል፡፡ከቀሪዎች ቁጥሮች አንፃር የኢያሱ ጥንካሬ የሚመጣው ከየት ነው ?

_________________________________________________________

_________________________________________________________

ሐ. ቁጥር 9 ላይ እግዚአብሄር ኢያሱን ________________________________እና ________________________________እንዲሆን ነገረው።የዚህ ተቃራኒው ምንድነው?______________እና______________።ለምንድነው ለፍርሀት እና ለሽብር እንዲሁም ተስፋ ለመቁረጥ ስፍራ የሌለው ለምንድነው?

4. በቁጥር 10 እና 11 ላይ ኢያሱ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ለህዝቡ ሰጠ በቁጥር 16 እና 18 ላይ የህዝቡ ምላሽ ምን ነበር?
   - *ያዘዝከንን ሁሉ እናደርጋለን*__________________________________________
   - *ወደላክን ሁሉ እንሄዳለን*______________________________________________
   - ለሙሴ *እንደታዘዝን እንደዚሁ ላንተም እንታዘዝልሀለን*______________________

   የበረከት ፀሎታቸውም____________________ከሙሴ ጋር እንደነበር።በኢያሱ አመራር ላይ ማመፅ ______________ያስቀጣል። እንደገና ለመሪያቸው የሰጡት የማበረታቻ ቃል እንዲህ የሚል ነበር____________

## ትምህርት አንድ -ክፍል 2

**ገለፃ፡**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተከናወነውን ነገር ለማንፀባረቅ ጥቂት ጊዜ ውሰዱ፡፡እግዚአብሄር ገና በመጀመሪያ ለአብርሀም የተስፋ ቃል ከሰጠበት ግዜ አንስቶ ብዙ ትውልድ ኖሯል እንዲሁም ሞቷል፡፡አብርሀም፣ልጁ ይስሀቅ፣እንዲሁም የልጅ ልጁ ያዕቆብ ሁሉም ሞተዋል፡፡ታላቁ የግብፅ መሪ የነበረው ዮሴፍ እና ወንዱሞቹም ሞተዋል ተስፋውም ለልጆቻቸው ተላልፏል፡፡እግዚአብሄርም ከግብፅ የጭቆና እና ከፈርኦን የባርነት አገዛዝ በኋላ ከግብፅ ሲወጡ እንዲመራቸው ሙሴን ሰጣቸው፡፡ነገር ግን ለአርባ አመት ያህል በምድረበዳ ሲቅበዘበዙ እንደገና ሌላ ትውልድ  በምድረበዳ አለቀ፡፡አሁን ሙሴ እራሱ ሞቷል፡፡

ነገር ግን አሁንም እግዚአብሄር አልተለወጠም፡፡እየፈፀመ ያለው ቃል የገባውን ነው፡፡ለተስፋው ፍፃሜ መሪን በማዘጋጀት ህልውናውን በመካከላቸው አደረገ፡፡ልክ ከባሮቹ ከአብርሀም እንዲሁም ከሙሴ ጋር እንደነበር  እንዲሁ ከኢያሱ እና ከህዝቡ ጋር ሆኗል፡፡የተስፋ ቃሉ የተሰጣቸው አባቶች ቆመው በዚያ ምስክር ባይሆኑም እግዚአብሄር ግን ታማኝነቱን ጠብቆ የገባውን የተስፋ ቃል ፈፅሟል፡፡እግዚአብሄር አላረጀም፣ አልረሳም፣ሃሳቡንም አልለወጠም፡፡ በራሱ ማንነት ላይ የተመሰረተውን መልካምነት ለህዝቡ በማሳየት ታማኝ ነው፡፡ስለዚህ እስራኤላውያን በቃሉ ላይ እንደተደገፉ እኛም ደግሞ ከብዙ ሺህ አመታት በኋላ በእግዚአብሄር ቃል ላይ ልንታመን ይገባናል፡፡

**ትግበራ፡**

“ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ ……..በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ አትፍራ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን? እውነት የሆነውን የእግዚአብሄርን ቃል በማመን ከዚህ ክፍል ለህይወታችሁ የቀረላችሁ ትምህርት ምንድነው?

________________________________________________

________________________________________________

**ፀሎት፡**

እግዚአብሄር አምላኬ ሆይ አንተ ለአብርሀም ተስፋ ስትገባለት እንደገና ለያዕቆብ ስታረጋግጥለት  ሙሴን ስትጠራው  ከእርሱ ጋር እንደሆንክ ለኢያሱ ስትነግረው በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ አንተ አልተለወጥክም፡፡ህልውናህ ከእኔ ጋር እንደ ሚሆነ ቃል የገባህልኝ ቃልኪዳንህንም ያረጋገጥክልኝ አንተ ነህ፡፡ስለማይለወጠው መልካምነትህ እና ታማኝነትህ እጅግ አመሰግንሀለሁ፡፡አንተ ለእኔ መልካም እና ታማኝ ነህ፡፡ልቤ በአንተ አርፏል ፈፅሞ ስላልተውከኝ እና ስላልረሳኸኝ አመሰግንሀለሁ፡፡

## <u>ትምህርት አንድ-ክፍል 3</u>

**መግቢያ:**

ኢያሱ 2 እስራኤላውያን ምድሪቱን ለመውረስ ዝግጅት አደረጉ፡፡ወደዚህ አዲስ እና እንግዳ ምድር ይህን ህዝብ መርታችሁ የምታስገቡት እናንተ ብትሆኑ ህዝቡን በምን መልክ ታዘጋጁት ነበር ? የተለያዩ የምድሪቱን ካርታ ፈልጋችሁ ትመለከቱ ነበር? ብዙ መረጃዎችን ታሰባስቡ ነበር ? ወይንስ ወደ ምድሪቱ ለመግባት የሚመራችሁ መፅሐፍ ትፈልጉ ነበር?

**የቤት ስራ:**

መፅሐፈ ኢያሱ 2 አንብቡ፡፡ከዚህ ክፍል የምታተኩሩባቸው ጥያቄዎች:

- ተልዕኮው ምን ነበር?
- ዋናው ገፀባህሪ ማነው?
- ሰላዮቹን በምን መልክ ነው የረዳቻቸው?
- ምን ነበር ያወቀችው?
- ስምምነታቸው ምን ነበር?
- ለኢያሱ የደረሰው መረጃ ምን ነበር?

**መልመጃ:**

ሰጢም ኢያሱ ለስለላ የተላከባት ስፍራ ነች፡፡በድሮው ካርታ ላይ ከሙት ባህር በስተሰሜን እንዲሁም ከኢያሪኮ በስተምስራቅ በኩል ትገኛለች፡፡

1. ተልእኮው ቀላል ነበር ፡፡ኢያሱ ሁለት ሰላዮችን ወደ______________ላከ የተለየ ፍላጎት የነበረው በ________________________________________ላይ ነበር (ቁጥር 1)፡፡ይህቺ ከተማ በቁጥጥር ስር የዋለች የመጀመሪያዋ ትልቋ ከተማ ነበረች፡፡
2. ይህን ክፍል ስታጠኑ ረአብ የሚለውን ቃል ስታገኙ በማስታወሻ ደብተራችሁ ፃፉ፡፡ ለምሳሌ እሷ ጋለሞታ ነበረች ነገር ግን ሰላዮችን በቤቷ ውስጥ ሸሸጋለች፡፡እስራኤላውያን ወደ እርሷ ቤት ሲቀርቡ እንዴት ነበር ምላሽ የሰጠችው? እሷ የሰጠችውን ምላሽ

ከኢያሪኮ ንጉስ ምላሽ ጋር አነፃፅሩት፡፡የእስራኤልን ሰላዮች ሸሸገቻቸው፣መንገድ መራቻቸው፣ከእነርሱ ጋር ተደራደረች፣በመሃላ ቃል አስገባቻቸው፣ከከተማውም እንዲያመልጡ ወደመጡበትም በደህና እንዲመለሱ እረዳቻቸው፡፡ምን አይነት ሴት እንደዚህ ልታደርግ ትችላለች? እስቲ ስለ ረአብ የበለጠ ተመልከቱ፡፡

ሀ. ከቁጥር 8-11 ባለው ክፍል ውስጥ ስለ ፍርሃት ፣የልብ መቅለጥ፣እንዲሁም ዋጋ የሌለው ማበረታታት የሚሉትን ቃላት በሙሉ ምልክት አድርጉባቸው፡፡

ለ. እስቲ ጥቂት ግዜ ውሰዱ እና በዘፀአት 15፡13-16 ያለውን ክፍል ተመልሳችሁ አንብቡት፡፡እስራኤል ቀይ ባህርን በደረቅ ምድር ተሻገሩ ይህንን ሙሴ እንዲሁም እስራኤላውያን ለእግዚአብሄር ካቀረቡት ዝማሬ መረዳት እንችላለን፡፡እነዚህ አራት ጥቅሶች በኢያሪኮ ምን እንደተከሰተ ይነግሩናል፡፡ስለ ፍልስጥኤማውያን፣ኤዶማውያን፣ሞአባውያ ፣እንዲሁም ከነአናውያን) ስለ "ፍርሃት" የሚናገሩትን ክፍሎች በሙሉ አስምሩባቸው፡፡

*ማስታወሻ፡* ስለከነአን መሸነፍ በሚናገረው ጥንታዊ ካርታ ላይ እነዚህ ህዝቦች ተገልፀዋል፡፡

ሐ. ረአብ ጠንካራ እና ብርቱ ሴት ናት፡፡ይህንን ብርታት እና ጥንካሬ ያስገኘላት ሊፈፀም ያለውን እውነታ በማወቋ ነበር፡፡

- እውነታ፡ ክስተቶቹ ምን ነበሩ (ቁጥር 10)?

  ______________________________________________

  ______________________________________________

- እውነታ፡ ስለእስራኤል ያወቀችው ምን ነበር (ቁጥር 11)?

  ______________________________________________

  ______________________________________________

3. በቁጥር 12-13 ባለው ክፍል ላይ ጥያቄዋ ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

ምላሻቸውስ ምን ነበር?______________________________________

4. ረአብ ማምለጥ የሚችሉበትን መንገድ በመምራት ረዳቻቸው፡፡ሰላዮቹም ከእርሷ ጋር የተነጋገሩት ቃል "ማንም ከአንቺ ጋር የሚኖር ሰው በቤት ውስጥ ከተገኘ ይጠበቃል ፡፡ ከቤት ውጪ ከተገኘ ግን ደሙ በራሱ ላይ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ይህን እኛ ከአንቺ ጋር የተነጋገርነውን ሚስጥር ለሌላ ሰው ከተናገርሽ ውላችን ይፈርሳል" የሚል ነበር፡፡
   ሀ. የረአብ ቤት መጠለያ ፣ማምለጫ እንዲሁም የማይደፈር መሸሸጊያ ሆነላቸው፡፡አንድ እንደ መቀነት ያለ ቀይ ጨርቅ የእርሷን ቤት መለያ ምልክት ተደርጎ በመስኮቷ በኩል ተሰቅሏል፡፡ሰላዮቹም የእርሷ ቤት እንደሚታለፍ ቃል ገብተውላታል፡፡
   ለ. በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በግብፅ እያሉ በምሽት የተፈፀመ ከማለፍ (ፋሲካ) ጋር የተያያዘ ክስተት ታስታውሳላችሁ? በጉበኑ ላይ የተቀባው ደም ትዝ ይላችኋል ? ይህ ደም ከመቀባቱ የተነሳም ሞት የማይቀርብበትን አደራረግ አስታወሳችሁ? ዘፀአት 12 ተመልከቱ፡፡
5. ሰላዮቹ ወደ ኢያሱ በደህና ተመለሱ፡፡
   ሀ. ያቀረቡት መረጃ ምን ነበር?____________________________________
   ለ. ምን አወጁ?____________________________________________

**ትግበራ፡**

ቁጥር 8 ላይ ረአብ ያወቀችውን ተናገረች እንደተረዳችውም አደረገች፡፡ እንዲህ አለች "……*እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደ ሰጣችሁ፥*" ሌላ ያወቀችውን ነገር እንደዚህ በማለት ተናገረች "*እናንተንም መፍራት በላያችን እንደ ወደቀ፥ በምድሪቱም የሚኖሩት ሁሉ ከፊታችሁ እንደ ቀለጡ አወቅሁ።*" እናንተስ ስላወቃችሁት ነገር እራሳችሁን ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ?

- ስለ አምላካችሁ እግዚአብሄር ያወቃችሁት እውነተኛ ነገር ምንድነው?

________________________________________________________

________________________________________________________

- ያወቃችሁት ነገር ብርታትን ለእናንተ የሰጠበት ወይንም ደግሞ በፍርሀት ልባችሁን ያቀለጠበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ሰላዮቹ እና ረአብ እግዚአብሄርን አውቀዋል ስለዚህም በጥንካሬ እና በትጋር ነበር የሚሰሩት፡፡ሰላዮቹ ለኢያሱ እንዲህ አሉት *"በእውነት እግዚአብሔር አገሩን ሁሉ በእጃችን አሳልፎ ሰጥቶአል በአገሩም ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ በፊታችን ይቀልጣሉ "*

## <u>ትምህርት አንድ -ክፍል 4</u>

***መግቢያ፡***

ሰላዮቹ የምስራች ይዘው ተመልሰዋል (ኢያሱ 2፡24) አሁን እስራኤላውያን በሴጢም ያለውን ሰፈራቸውን ለቀው በዮርዳኖስ ወንዝ የሚሰፍሩበት ግዜ መጥቷል፡፡ቀጣዮቹ ሶስት ምዕራፎች ስለዚህ ጉዳይ ዝርዝር ነገር ይሰጣሉ እኛ ግን በዚህ ጥናት በአራት ነገሮች ላይ እናተኩራለን፡፡

1. የዮርዳኖስን ወንዝ ማቋረጥ
2. የቃልኪዳኑ  ታቦት
3. የእስራኤል ማህበር
4. የግርዛት ቃልኪዳን

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 3-4፡24 ያለውን ክፍል በጥንቃቄ በማንበብ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከቱ

- ለህዝቡ የተሰጡ  ትእዛዛት
- የቃልኪዳኑ ታቦት ሚና
- ለእስራኤል የተሰጠ እውቅና

***መልመጃ፡***

1. ለህዝቡ የተሰጡት ትእዛዛት ምን ነበሩ
   - 3፡3__________________________________________________
   - 3፡5__________________________________________________
   - 3፡9__________________________________________________
2. የቃልኪዳኑ ታቦት ከህዝቡ ፊት ይሄዳል አሁን ግን ህዝቡን በምድረበዳ ሲመራ ስለነበረው የእሳት እና የደመና አምድ ምንም አልሰማንም፡፡እስቲ በቃልኪዳኑ ታቦት ውስጥ ምን እንደተቀመጠ አስታውሱ ዕብራዊያን 9፡4 ›________________________እና

_________________________ነበሩ፥ታቦቱ ለህዝቡ የእግዚአብሄርን ህልውና በመወከል በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ይቀመጣል፡፡

ሀ. (ቁጥር 3)-የቃልኪዳኑን ታቦት የሚሸከመው ማነው?_________________________

ለ. የህዝቡ ድርሻ ምን ነበር?_________________________________________________

ሐ. (ቁጥር 4) -ህዝቡ የሚያውቀው ምን ነበር?________________________________

መ. ልዩው ትእዛዝ ምን ነበር?______________________________________________

**<u>ትምህርት አንድ-ክፍል 5</u>**

**ትምህርት፡**

"ማህበር" የሚለውን ቃል አስቡ፡፡ይህ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን የሚያራምድ የራሱን ፈቃድ የሚያደርግ ህዝብ አይደለም፣ እጁን በማውጣት በምርጫ የሚሾም እና የሚሽር አይደለም፡፡ነገር ግን በመለኮታዊ አገዛዝ ስርአት ከእግዚብሄር ትእዛዝ እየተቀበለ የሚኖር ህዝብ ነው፡፡የሚሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ እያደረጉ የእርሱ ህዝብ ሆነው ነው የሚኖሩት፡፡

በምድረበዳው ጉዞአቸው እግዚአብሄር እርሱ አምላካቸው እነርሱ ደግሞ የእርሱ ህዝብ ሆነው እንደሚኖሩ ለአብርሀም የገባውን ቃልኪዳን ያስታውሳቸው ነበር፡፡ታላቁን ጥሪ በመቀበል ቅዱስ እና ለእርሱ በተሰጠ እንዲሁም በታማኝነት ህይወት ለጠራቸው ጥሪ እና አላማ እንዲኖሩለት ነው የጠራቸው፡፡ለእነርሱ ያለው ፍቅር አይወድቅም፡፡ከህዝቡ መካከል አንዳንዶች ሲያጉረመርሙ እና ኃጢአታቸው ያመጣባቸውን ቅጣት ሲቀበሉ ተመልክተናል (ዘኁልቁ 14፡34-35)፡፡እግዚአብሄርን ሲበድሉ ሁሉም ሰው የኃጢአቱን ውጤት ይቀምሳል(ዘፀአት 32፡19-20) እግዚአብሄር አስርቱን ትእዛዛት ሲሰጣቸው ሲታዘዙ እንደሚባረኩ ሳይታዘዙ ሲቀሩ ደግሞ እርግማን እንደሚያገኛቸው ቀድሞውኑ አሳውቋቸዋል፡፡ከዚህ ስርአት ውጪ የሚኖር የለም፡፡የዚህ ማህበር አካል የሆነ ሁሉ የሚስተናገደው በዚህ መልክ ነው፡፡

**መልመጃ፡**

ቀጥሎ በተዘረዘሩት ክፍሎች ውስጥ ህዝቡ በማህበር እንጂ በተናጠል መኖር እንደማይችሉ የሚያመለክቱ ቃላቶችን ለይታችሁ አውጡ፡፡አንድን ማህበር ሊያመለክቱ የሚችሉ "ሁሉም" እና "በመካከላቸው" የሚሉትን አይነት ቃላት የሚመስሉ ፈልጉ፡፡

| ጥቅሶች | ማህበር የሚያመለክቱ ቃላት |
|---|---|
| ኢያሱ 3፡5 | |
| ኢያሱ 3፡9፣10 | |
| ኢያሱ 4፡1 | |
| ኢያሱ 4፡4-7 | |

| | |
|---|---|
| ኢያሱ 4፡13 | |
| ኢያሱ 4፡14 | |

**ትግበራ፡**

እያንዳንዳችን የአንድ ማህበረሰብ አካል መሆን እንፈልጋለን፡፡በአብዛኛው ሰዎቸ በቤተሰባዊ ህብረት ውስጥ ነው የተወለዱት፡፡በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ እናድጋለን ለምሳሌ ትምህርትቤት፣ቤተክርስትያን፣የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የምንሰጥባቸው ድርጅቶች፡፡የማህበረሰብ አካል እንደመሆናችን የአላማ፣የወግ እንዲሁም ስነምግባራዊ መዋቅሮችን ተስማምተንባቸው እንኖራለን፡፡እስኪ እናንተ የኖራችሁበትን ማንበረሰባዊ ሁኔታ ግለፁ፡፡

- የዚያ ማህበረሰብ አካል የሆናችሁት እንዴት ነው? መቼ ነው የዚያ ማህበረሰብ አካል እንደሆናችሁ የተሰማችሁ?

  ________________________________________________________

- የዚህ ማህበረሰብ አላማ ምንድነው? ለምንድነው ይህ ማህበረሰብ መኖር ያስፈለገው?

  ________________________________________________________

  ________________________________________________________

- በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያበረከታችሁት አስተዋፅኦ እንዲሁም የተሳተፋችሁት ተሳትፎ ምን ይመስላል? ማህበረሰቡስ ለእናንተ ያለው ስፍራ ምን ይመስላል?

  ________________________________________________________

  ________________________________________________________

## <u>ትምህርት ሁለት-ክፍል 1</u>

**የቤት ስራ፡** ዘፍጥረት 17፡7-14 እንዲሁም ኢያሱ 5፡1-12 ያለውን ክፍል አንብቡ

**ትምህርት፡**

በዘፍጥረት ላይ ያለው ምንባብ እግዚአብሄር ለአብርሀም እና ለዘሩ አምላክ ሊሆን ቃል የገባበትን ዘላለማዊ ቃልኪዳን ያስነብበናል፡፡በእግዚአብሄር አነሳሽነት የመጣው ቃልኪዳን በእርሱ እና በህዝቡ መካከል ግንኙነት መስርቷል፡፡ እርሱ አምላካቸው ይሆናል እነርሱ ደግሞ ህዝቦቹ፡፡በአብርሀም እና በእግዚአብሄር መካከል ለተመሰረተው ለዚህ ግንኙነት ምልክቱ የወንዶች የግርዘት ስረአት ነበር፡፡ኢያሱ 3-5 የእስራኤልን ታሪካዊ ወቅት ያሳየናል፤ እግዚአብሄር በዘፍጥረት 17፡8 ላይ ለአብርሀም ከነአንን ለእርሱ እና ለዘሩ የዘላለም እርስት አድርጎ እንደሚሰጠው ቃል የገባለት መሆኑ አይነጋም፡፡

በኢያሱ 5፡1-12 ባለው ክፍል ውስጥ ሁለት ማህበራዊ ክስተቶች ተከስተዋል፡፡የመጀመሪያው እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡበት ግዜ ጀምሮ በምድረበዳ የተወለዱት ወንዶች በሙሉ መገረዛቸው ሲሆን፡፡የግርዘት ስርአት "እግዚአብሄር አምላካችን ነው እኛንም በዘላለም ቃልኪዳን የእርሱ ህዝቦች እንሆን ዘንድ ተለይተናል" የሚልን አዋጅን የሚያውጅ ነው፡፡ ግርዘት ለህዝቡ የሚያስተላልፈው መልእክት በእራሱ በእግዚአብሄር ለተመሰረተው ማህበር ተለይተን የእግዚአብሄር ሆነናል የሚል ነው፡፡ያልተገረዘ ደግሞ ከዚህ ህዝብ ተለይቶ ጠፍቷል የዘላለሙ ቃልኪዳን አካል አይደለም ማለት ነው፡፡

ሌላው የዚህ ማህበር መለያ የፋሲካ በአል አከባበር ነው፡፡ይህን በአል ማክበር የመታዘዝ ምልክት ነው፡፡በግብፅ እያሉ በእግዚአብሄር ፋሲካ እለት የበጉ ደም በጉበኑ ላይ ሲቀባ የተከሰተውን ያውቃሉ (ዘፀአት 12) ፡፡የፋሲካው የምግብ ስርአትም በሚቀጥለውም ትውልድ በተመሳሳይ መልክ መደረግ አለበት፡፡ዘፀአት 12፡24-24 ወደ ተስፋይቱ ምድር ከነአን ሲገቡም ይህንን ስርአት ታዘው እንደሚፈፅሙ በግልፅ ይናገራል፡፡

***መግቢያ***

*አሁን ደግሞ በደንብ የምናውቀውን የጦርነት ታሪክ ልንመለከት ነው፡፡ስለዚህ ጦርነት መዝሙሮች ተዘምረዋል፡፡ ልጆችም ይህንን ታሪክ ተምረውታል፡፡በትምህርት ቤትም የተለያዩ ጨዋታዎችም ተሰርተውበታል፡፡ይህ በብሉይ ኪዳን የተካሄደ ጦርነት የሚገኘው በኢያሱ 6 ላይ ነው፡፡*

*እስራኤላውያን ስፍራቸውን ይዘው ቆመዋል፡፡እራሳቸውን ለእግዚአብሄር አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡እግዚአብሄር ካዘጋጀላቸው የበረከት ክምችት አስደናቂ ነገሮችን ለመቀበል ተዘጋችተዋል ፡፡ ዮርዳኖስን ለመሻገር የቃልኪዳኑ ታቦት እስኪመራቸው እየጠበቁ ነው፡፡ አሁንም እንደገና እስራኤላውያን ወንዙ ፍሰቱን አቁሞ በደረቅ ምድር ተሻገሩ፡፡ዮርዳኖስን እንደተሻገሩ የእስራኤል ወንዶች ሁሉ ተገረዙ፣የፋሲካንም በአል በእያሪኮ ሜዳ በጌልጌላ አከበሩ ፡፡አሁን የምድሪቱን ፍሬ መመገብ ስለጀመሩ መና መውረድ አቁሚል፡፡*

*የእግዚአብሄር ህዝብ ምግብ ተመግበዋል ፣እረፍት አድርገዋል፣ዘና ብለዋል ስለዚ አሁን በኢያሪኮ ላለው ጦርነት ተዘጋጅተዋል፡፡ ኢያሱ ልክ እንደሙሴ ከእግዚአብሄር ጋር መነጋገር ለምዷል ዘፀአት 3፡5፡፡እግዚአብሄር አብሮት እንዳለ ምንም አይነት ጥርጣሬ እንዲኖረው አልፈለገም ወይንም ደግሞ የእግዚአብሄር ሰራዊት መሪ መሆኑን እንዲጠራጠር እግዚአብሄር አልፈለገም፡፡ኢያሱ በፊቱ መሬት ላይ ተደፍቶ ለእግዚአብሄር ክብር መስጠት ብቻ ነው ያለበት፡፡*

***የቤት ስራ፡***

*ኢያሱ 6 ስታነቡ ከዚህ በታች ያሉትን ነገሮች ልብ በሉ፡*

- *የእግዚአብሄር እቅድ*
- *የኢያሱ መመሪያዎች*
- *የእስራኤል እቅድ አፈፃም*
- *ኢያሱ ስለ ረአብን እና በሙሉ ልባቸው ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች አስጠነቀቀ*
- *የረአብ መዳን እና የኢያሪኮ መፍረስ*
- *ኢያሱ ኢያሪኮን መርገሙ*

<u>**ትምህርት ሁለት-ክፍል 2**</u>

**መልመጃ:**

1. በቁጥር 1 አና 2 ላይ እግዚአብሄር ለኢያሱ የገለጠለት ምንድነው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ኢያሪኮን በእስራኤላውያን እጅ አሳልፎ ሰጥቷቸዋል፡፡ፍርሃታቸው ከምን የመነጨ ነበር? እስራኤላውያን ምን ነበር ያደረጉት? እግዚአብሄር ያደረገውን ነው? ኢያሱ 5፡1 አንብቡ፡፡

________________________________________________________

2. በቀላሉ የእግዚአብሄር እቅድ ምን ነበር? (እያሱ 6፡3-5)

ሀ.የታጠቁት ሰዎች ምን እንዲያደርጉ ነው የተነገራቸው?______________________

ለ. ሰባቱ ካህናትስ?_________________________________________________

በሰባተኛው ቀን ምን ነበር ያደረጉት?____________________________________

ሐ .ህዝቡስ ምን ያደርጋሉ?____________________________________________

________________________________________________________

________________________________________________________

መ. ግንቡስ ምን ይሆናል?

________________________________________________________

________________________________________________________

የሰባቱ ካህናት የታጠቁ አጃቢዎች በሙሉ ህዝቡ እንዲንቀሳቀስ መለከት ይነፋሉ፡፡ የቃልኪዳኑን ታቦት የተሸከሙት ቀድመው ሲሄዱ ህዝቡ ደግሞ በተወሰነ እርቀት ታቦቱን አጅቦ ይከተላል፡፡

ሀ. በቁጥር 10 ላይ ኢያሱ ለህዝቡ የሰጠው የተለየ ትእዛዝ ምንድነው ?

1. ______________________________________ አታድርጉ
2. ______________________________________ አታድርጉ
3. ______________________________________ አታድርጉ

ለ. ህዝቡ ኢያሪኮን አንዴ ከዞሩ በኂላ ወደ ሰፈራቸው ይመለሳሉ!እንዴት ልዩ የሆነ ትእይንት ነው!ይህንንም ድርጊት ለስድስት ቀን ደጋገሙት!

1. የኢያሪኮ ንጉስ ብትሆኑ በአእምሮአችሁ ውስጥ ምን ይመላለስ ነበር?

   ______________________________________

2. ከኢያሪኮ ነዋሪዎች አንዱን ብትሆኑ ወይንም የዚያች ሃገር ወታደር ብትሆኑ ግንቡን እየዞሩ ያሉትን እስራኤላውያንን በቅጥሩ ላይ በሚገኝ አንድ ቀዳዳ ብትመለከቱ በአእምሮአችሁ ውስጥ ምን አይነት ነገር ይመላለሳል?

   ______________________________________

   ______________________________________

3. ረአብን ብትሆኑ እና ከዘመድ አዝማዶቻችሁ ጋር በቤት ውስጥ ተሰብስባችሁ ከሰላዮቹ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል ይዛችሁ በውጪ ያለውን ምድር የሚያንቀጠቅጥ ሰራዊት ስትመለከቱ ምን ይሰማችኂል?

   ______________________________________

   ______________________________________

ሐ. ነገር ግን የሰባተኛው ቀን ልዩ ነበር፡፡ይህንን ቀን ልዮ ያደረገው ምን ነበር?

______________________________________

______________________________________

ካህናቱ የመለከቱን ድምፅ ሲያሰሙ ምን ሆነ? በሚከተሉት ቁጥሮች ላይ የኢያሱ ትእዛዝ ምን ነበር?

- ቁጥር 16? ______________________________
- ቁጥር 17? ______________________________

- ቁጥር 18-19? ________________________________________

4. ቀጥሎ ድል መጣ! ህዝቡ የጩኸት ድምፁን አሰማ፡፡ግንቡም ከድምፁ የተነሳ ተናደ እስራኤላውያንም ከተማይቱን ተቆጣጠሩ (ቁጥር 20) ፡፡ህይወት ያለውን ነገር ሁሉ ገደሉ፡፡በከተማይቱ ያገኙትን ብር፣ወርቅ፣ነሐስ፣እንዲሁም ብረቱን ምን አደረጉት?

________________________________________

________________________________________

ረአብ እና ቤተሰቧስ ምን ገጠማቸው?________________________________

________________________________________

5. ቁጥር 26-27 ላይ ኢያሱ ኢያሪኮን መልሶ የሚሰራ የተረገመ ይሁን ብሎ ረገመ ፡፡በቁጥር 26 ላይ “በር” ለሚለው ቃል ማጣቀሻ ቁጥሮችን የሚፈልግ ማጣቀሻዎችን ማየት ይችላል፡፡
*ማስታወሻ፡* መፅሐፍ ቅዱሳችሁ ማጣቀሻ ከሌለው ለዚህ ቁጥር የሚሆነው ማጣቀሻ (1ነገስት 16፡34) መመልከት ትችላላችሁ፡፡

## ትምህርት ሁለት- ክፍል 3

**ገለፃ**

ለእስራኤል እንዴት አይነት ድል ነው! ምድሪቱን መውረስ እንዲህ ቀላል ከሆነ ቀሪዎቹም ውጊያዎች ልክ ከአንድ ሰው እጅ የተቆረሰ ኬክን የመቀበል ያክል ቀላል ናቸው ማለት ነው፡፡ ማድረግ ያለባቸው የቃልኪዳኑን ታቦት መከተል ፣የመለከቱን ድምፅ መስማት ከዛም መጮህ ነው፡፡በእርግጥ ግንቡን የጣለው ጩኸቱ አይደለም፡፡ነገር ግን እግዚአብሄር የህዝቡን ጥንካሬ በመጠቀም ትእዛዙን ለመጠበቃቸው ምላሽ በመስጠት ውጊያቸውን ይዋጋላቸዋል፡፡እግዚአብሄር ይህን ሁሉ የሚያደርገው አምላካቸው ስለሆነ እነርሱም የእርሱ ህዝቦች ስለሆኑ ነው፡፡ዓለም ሁሉ እርሱ የእስራኤል አምላክ እና መሪያቸው መሆኑን እንዲያውቅ ነው፡፡

**ትግበራ**

ረአብን እናስባት፡

1. በብቸኛው የደህንነት ተስፋዋ ላይ ታምና ተቀምጣለች፡፡እናንተስ የደህንነታችሁ ተስፋ በምን ላይ የተመሰረተ ነው?

   ______________________________________________

2. ባደረገችው መሃላ መሰረት ቃሏን በመጠበቋ ምክንያት እራሷን እና ቤተሰቧን ማዳን ችላለች፡፡እናንተስ በምን አይነት መልኩ ነው ለቤተሰቦቻችሁ፣ ለጓደኞቻችሁ ፣እንዲሁም ለጎረቤቶቻችሁ የደህንነት ምክንያት የምትሆኑት ?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

3. ዕብራውያን 11፡30-31 አንብቡት፡፡ በዚህ ስፍራ ስለ ረአብ የተነገረው ምንድነው?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

እምነቷን በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሄር ላይ ስላደረገች እንደዚሁም ሰላዮቹን ተቀብላ ስላስተናገደች እግዚአብሄር መልካም አደረገላት፡፡እስቲ የእግዚአብሄርን መልካምነት በህይወታችሁ አስቡ፡፡

**ትምህርት፡**

በቀይ ባህር ውስጥ ማለፍ እንዲሁም በዮርዳኖስን ወንዝ ውስጥ በደረቅ ምድር ማለፍ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ በጣም ጠቃሚ የሆነን ወቅት ያስታውሰናል፡፡በመጀመሪያ ቀይባህርን ሲሻገሩ በግብፅ ያለው የባርነት ዘመናቸው አበቃ፡፡የግብፅ ሰራዊት በቀይ ባህር ሰጠመ እስራኤላውያንም ጉዞአቸውን ወደ ተስፋይቱ ምድር ቀጠሉ፡፡አዲስ ህይወት ከፊታቸው ይጠብቃቸዋል፡፡እግዚአብሄርም እርሱ አምላካቸው እነርሱም ህዝቦቹ እንደሆኑ ያስታውሳቸዋል፡፡ እራኤላውያን እንደ ማህበር ሲኖሩ ከእግዚአብሄር መመሪያ ተሰጥቶአቸዋል ፡፡ እግዚአብሄር በእነርሱ ላይ ያለው ስልጣን የባሪያ አሳዳሪ አይነት ሳይሆን የመሪነት ስልጣን ነው፡፡በፍርሀት የሚከተሉት አምላክ ሳይሆን የሚወዱት እና የሚያምኑት ፣ የሚታዘዙት እና የሚያገለግሉት አምላክ ነው ፡፡ ከእግዚአብሄር ጋር ያላቸው ግንኙነት በፍቅር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ነው፡፡ለህዝቡ ሁልግዜ መልካም ነው የሚያስበው፡፡

እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገሩ አላማ የለሽ እና መቅበዝበዝ የሞላበትን ህይወት፣ በአለመታዘዛቸው ምክንያት የሚመጣባቸውን ቁጣ በሙሉ በኂላቸው ጥለው ነበር የተሻገሩት፡፡አንድ ልብ ያላቸው በዘላለም ቃልኪዳን ቃል የተገባላቸውን ምድር ለመውረስ የተዘጋጁ ህዝቦች አድርጎ ቀርፆአቸዋል፡፡

ይህ በውሃ ውስጥ መሻገር በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ጠቀሜታ ያለው ክስተት ነው፡፡ (በማቴዎስ 3፡13) ላይ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ ተመሳሳይ ነገር ተፈፅሟል፡፡ እንደገናም በማቴዎስ 28፡19 ላይ በእርሱ የሚያምኑ ህዝቦች በሙሉ በተመሳሳይ መልኩ እንዲጠመቁ ነግሮአቸዋል፡፡የቀደመችው ቤተክርስትያን የተመሰረተችው ደቀመዛሙርቱ ወንጌልን እየሰበኩ እና በኢየሱስ ስም እያጠመቁ በቀጠሉት መንገድ ነው (የሐዋሪያት ሥራ 2፡38) ፡፡የጥምቀት ስርአት መስራች እግዚአብሄር ነው፡፡እግዚአብሄር ለእኛ የኃጢአትን ስርየት እንዲሁም የዘላለምን ህይወት በመስጠት መርጦናል፡፡በጥምቀት ውስጥ በማለፋችንም በዘላለም

ቃልኪዳን እርሱ የእኛ አምላክ እኛም የእርሱ ህዝቦች መሆናችንን አውጆናል፡፡የኃጢአት ባርያ የመሆን ዘመን አብቅቷል ፣ በእግዚአብሄር በተመሰረተልን የፍቅር ግንኙነት የዘላለም ይቅርታ እና በነፃነት መኖርን ሆኖልናል፣ ተዋጅተናል፣ህይወታችን እንደገና በእግዚአብሄር ተመልሷል፣ በዋጋ ተገዝተናል ዋጋችንም የእግዚአብሄር በግ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ፣ትንሳኤ ፣እና ህይወት ነው፡፡እግዚአብሄር በእኛ ውስጥ መኖር መርጧል፡፡ሰውነታችን የእርሱ መኖሪያ ሆኗል፡፡

የጥምቀትን ስርአት ፈፅማችኋል ? ወይንስ ጥምቀት ለእናንተ አዲስ ነገር ነው? በጥምቀት ውስጥ እግዚአብሄር ለእናንተ ስላዘጋጀላችሁ ነገር ታውቃላችሁ?________________

______________________________________________________________

አምናችሁ ስትጠመቁ ዓላማ እና ትርጉም ያለው ህይወት ይኖራችኋል፣የንጉስም ልጅ ትሆናላችሁ፡፡

## <u>ትምህርት ሁለት-ክፍል 4</u>

### *መግቢያ*

ኢያሪኮ ከገቡ በኋላ የተቆጣጠሩትን መሬት መውረስ ከላይ እንደተነጋገርነው ልክ ኬክ እንደመቁረስ ቀላል መስሎ ሊታይ ይችላል፡፡ኢያሱ ምዕራፍ 7 እንደሚነግረን በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ከሚኖሩት ሰዎች ጋር ምንም አይነት ውጊያ አላደረጉም ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች በተናጠል ባለመታዘዛቸው እና በሚበድሉት በደል ምክንያት ህዝቡ በጦርነት ጉዳት ይደርስበት ነበር፡፡

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 7 አንብባችሁ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከቱ፡፡

- ስህተት  የሆነው ነገር ምን ነበር?
- ጥፋተኛ ማን ነበር?
- ያስከተሉት ነገር ምን ነበር?
- ቅጣቱስ ምን ነበር?

***መልመጃ፡***

1. እስራኤላውያን በኢያሪኮ ላይ ያገኙት ድል በምእራፍ 6 ላይ ተጠናቋል፡፡አሁን ኢያሱ 7፡1 አንድ ክፉ ዜና ይነግረናል፡፡የተፈጠረው ነገር ምን ነበር?
    - ክፉ ያደረገው ማን ነበር?________________________________________
    - ምን ነበር የሸሸገው?____________________________________________
    - የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበር?____________________________________
2. እስቲ በቅርበት ተመልከቱት፡
    - አካን ጥፋተኛ ነበር? ይህ ክፍል ታማኝ ያልሆነው ማን እንደሆነ ነው የሚነግረን?

__________________________________________________________

- የእግዚአብሄር ቁጣ የነደደው በማን ላይ ነው?____________________________

  ባለፈው ትምህርታችን ላይ እግዚአብሄር እስራኤልን እንደ አንድ ማህበረሰብ እንደቆጠረው መመልከታችንን እናስታውሳለን፡፡በዚህም ምክንያት እግዚአብሄር እስራኤላውያን እንደበደሉ ነው የቆጠረው፡፡አካን የዚያ ማህበረሰብ አካል ነው ስለዚህ አካን የበደለውን በደል እግዚአብሄር እስራኤል በሙሉ እንደበደለ ነው የቆጠረው፡፡

3. የአንድ ሰው በደል በህዝቡ መካከል ምን እንዲከሰት አንዳደረገ እስቲ ታሪኩን ተከታተሉ፡
   - ኢያሱ እስራኤላውያን ቀጥሎ የሚወርሱትን ምድር እየተመለከተ ነበር፡፡ሰላዮችን የላከው ወዴት ነበር ቁጥር 2?

     ______________________________________________________________

   - በቁጥር 3 ላይ ሰላዮቹ ለኢያሱ ምን አይነት መረጃ አቀረቡለት? የሰጡትስ አስተያየት ምን ነበር?

     ______________________________________________________________

     ______________________________________________________________

4. ወደ ውጊያ ሄዱ
   - በቁጥር 4-5 ላይ ምን ተፈጠረ?

     ______________________________________________________________

     ______________________________________________________________

   - በህዝቡ ልብ ምን ተፈጠረ?

     ______________________________________________________________

   - የኢያሱ እና የሽማግሌዎች መልስ፡ በንስሀ፣ ልብሶቻቸውን ቀደዱ፡፡በፊታቸው ምድር ላይ ተደፍተው በላያቸው ላይ አቧራ ነሰነሱ፡፡
   - በቁጥር 7-9 የኢያሱን ፀሎት ተመልከቱ፡
     - ስለምን______________________________________________
     - ይህን ካደረጋችሁ ብቻ_______________________________________

- ምን ልላችሁ እችላለሁ______________________________________
- ከነአናውያን እና ሌሎች______________________________________
- ጥያቄ:__________________________________________________

- እግዚአብሄር ኢያሱን ምን አለው ? እስራኤላውያን ያደረጉትስ ኃጢአት ምን ነበር?
  - ______________________________________________________
  - ______________________________________________________
  - ______________________________________________________
  - ______________________________________________________
  - ______________________________________________________

- ከኃጢአታቸው በተጨማሪ በጦርነቱ ላይ ያደረጉት ነገር ምን ነበር (ቁጥር 12) ?

  __________________________________________________________

- ከዚህ ሁሉ ነገር በላይ እግዚአብሄር በቁጥር 12 ላይ የገለፀው ነገር ምን ነበር?

  __________________________________________________________

- ኢያሱ 6፡18 አንብቡት በዚህ ክፍል ውስጥ ኢያሱ ለህዝቡ የሰጠው መመሪያ እና ማስጠንቀቂያ ምንድነው?

  __________________________________________________________

  __________________________________________________________

- በቁጥር 13-15 ላይ ኢያሱ ህዝቡን እርም የሆነውን ነገር ፈልገው ከመካከላቸው እንዲያስወግዱ መመሪያ ሰጣቸው፡፡እርሱም የእግዚአብሄር ህግ እንደተጣሰ እና እንደተዋረደ ለህዝቡ አስታወቀ፡፡እግዚብሄር ለእርሱ እንዲሆኑ የለያቸው ነገሮች ናቸው አሁን ፈፅመው እንዲጠፉ ትእዛዝ ያወጣባቸው፡፡

- ኢያሱ ባጠፋው ሰው ላይ የከፋ ነገር እንደሚሆንበት ነገራቸው፡፡በማለዳም አክአን ተገኘ፡፡እርም በሆኑት ነገሮች ላይ ምን እርምጃ ተወሰደባቸው?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

- የተገኙትንም ነገሮች በሙሉ ወደ ኢያሱ አመጧቸው፡፡ኃጢአቱ በእስራኤላውያን ሁሉ ፊት ተገለጠ፡፡ቅጣቱን እስራኤላውያን በሙሉ ናቸው የተቀጡት፡፡ቁጥር 24-26 ምን ይነግሩናል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ትምህርት ሁለት-ክፍል 5

**ትግበራ፡**

የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው ። አካን፣ቤተሰቡ፣ እንዲሁም ንብረቱ በሙሉ በድንጋይ ተወገሩ ፣ በእሳት ተቃጥለውም ተቀበሩ ። ከህዝቡ መካከል ኃጢአትን ለማስወገድ እርሙ ፈፅሞ መወገድ አለበት።

1. ብዙ ግዜ ኃጢአትን እንድንደብቅ ወይንም እንድንሸፍን እንፈተናለን።ሰው ገድለን እንደቀበርን እንደብቃለን።በህይወቴ ውስጥ ሚስጥር አድርጌ የያዝኳቸው ኃጢአቶች ምንድናቸው? ከምንጣፌ በታች የደበቅኳቸው ኃጢአቶች ምንድናቸው?

   ________________________________________

   ________________________________________

2. እንደ ህዝብ ኃጢአትን እንዴት ነው የምናስበው?

   ________________________________________

   ________________________________________

3. በድብቅ የሰራሁት ኃጢአት ቤተሰቤን ፣ጓደኞቼን፣እንዲሁም ህዝቤን የጎዳው በምን መልኩ ነው?

   ________________________________________

   ________________________________________

**ፀሎት፡**

ጌታ ሆይ እንደ ህዝብ ኃጢአታችንን በፊትህ እንናዘዛለን።የበደልነውን በደል እንዳልበደለ በመሆን ኃጢአት ማድረጋችንን እንክዳለን።ወደ ኃጢአት የሚመሩንን ጠላቶቻችንን ለመዋጋት

ሰንፈናል።መልካም ከማድረግ ይልቅ ክፉ ለማድረግ እራሳችንን አሳልፈን ሰጥተናል።እባክህ ይቅር በለን።ምህረትንህ በእኛ ላይ ይሁን።እባክህ የካድነውን፣ያላስወገድነውን፣ቸል ያልነው እና የደበቅነውን ኃጢአት ይቅር በለን።ከማይረባ ፣ እፍረት እና ውርደት ከሞላበት ኑሮ አውጥተህ ፀጋህን እና ምህረትህን ስጠን።

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**መግቢያ፡**

አካን እና እርሙ ተገኝተዋል።እርሱ እና የእርሱ የሆኑት በሙሉ ከእስራኤል ህዝብ መካከል ተወግደዋል።በድንጋይ ተወግረው ፣ተቃጥለው ተቀብረዋል የእግዚአብሄር ቁጣም ከእስራኤል ላይ ተመልሷል።እግዚአብሄር ህዝቡን ይቅር አለ።የእስራኤል ህዝብ አሁን ከኃጢአት ነፅቷል፣እግዚአብሄር እንደገና ማካካሻ ሰጥቷቸዋል፣ሽንፈትም ከእስራኤላውያን ዘንድ ቆሟል። እናንተ ኢያሱን ብትሆኑ ኖሮ በጋይ ሰዎች ከደረሰባችሁ ሽንፈት የተነሳ ዳግም ወደ ውጊያ ስትወጡ በፍርሃት ታቅማሙ ይሆን?

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 8፡1-29 ያለውን ክፍል አንብቡ፡

**መልመጃ፡**

1. በቁጥር 1 እና 2 ላይ እግዚአብሄር ለኢያሱ ያዘዘው ነገር ምን ነበር?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

2. ጋይን ለመቆጣጠር የተያዘው እቅድ ምን ነበር ቁጥር 3-8?

______________________________________________

______________________________________________

3. ውጤቱስ ምን ነበር ቁጥር 9-29?

______________________________________________

______________________________________________

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 8፡30-35 ያለውን ክፍል እንዲሁም ዘፀአት 11፡26-32 አንብቡ፡፡

**መልመጃ፡**

- እስራኤላውያን ከጋይ በስተ ሰሜን ተጓዙ፡፡ለአስራሁለቱ ነገዶች የተደለደለው ስፍራ በሚያሳየው ካርታ ላይ የጌባልን እና የገሪዛን ተራራ ጠቁሙ፡፡
- ቁጥር 30 ኢያሱ ምን ገነባ? ______________________
  - ስለ መሰዊያ የተነገረን ምንድነው?______________________
  - በዘፀአት 20፡25 ላይ የተጠቀሱትን ማጣቀሻዎች ተመልከቱ፡፡ከዚህ ክፍል ምን ተጨማሪ ነገር እንማራለን? ______________________
- ለእግዚአብሄር መስዋእት አቀረቡ፡፡ኢያሱ ቀጥሎ በቁጥር 32 ላይ ያደረገው ምንድነው?

  ______________________________________________

  እስቲ ትእይንቱን በአይነ ህሊናችሁ አስቡት፡ እስራኤላውያን በከፊል በጌባል ተራራ ፊት ለፊት ቆመዋል ዘዳግም 27፡12፡፡ በመካከላቸው የቃኪዳኑ ታቦት እና ሌዋውያን ካህናት አሉ ኢያሱ በሁሉ ፊት የሙሴን ህግ በድንጋይ ላይ ፅፎታል፡፡ ለምንድነው እንዲህ ያደረገው? ብለን ልንጠይቅ አንችላለን፡፡ይህ ማጣቀሻ ወደ ዘዳግም 27፡8 ይወስደናል፡፡

- በ *መፅሀፈ ኢያሱ* 8፡34 ላይ እያሱ ምን አደረገ?

______________________________________________

______________________________________________

**ትምህርት፡**

ይህ ነገር የተከናወነው በእነዚህ ሁለት ተራሮች መካከል ነው፡፡ እነዚህ ተራሮች ህዝቡ ከእግዚአብሄር ጋር ላደረገው ቃልኪዳን ምስክሮች ናቸው፡፡ ይህ ቃል ኪዳንን ማደስ ነው፡፡ የተጠመቁ ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ሁል ግዜ በእግዚአብሄር ቃልኪዳን ይታደሳሉ፡፡ያለፈው በደል ሁሉ ተደምስሷል የሚመጣውም ዘመን የነፃት ነው፡፡እግዚአብሄር ከህልውናው እና ከሰጠን ተስፋ የተነሳ ሁል ግዜ አዲስ ጅማሬን በህይወታችን ይሰጠናል፡፡በኤርሚያስ ትንቢት ነቢዩ እንዲህ እያለ *ያሳስበናል፡"መተላለፋቸውን ይቅር እላለሁ ኃጢአታቸውንም አላስብም ይላል"* እንዴት ደስ የሚል የምስራች ነው!

## ትምህርት ሶስት-ክፍል 1

**ገለፃ፡**

ለራሳችሁ ታማኝ በመሆን እንዲህ አስቡ፡፡የአንዱ ነገድ አባል እንደሆናችሁ እና ከእነዚህ ተራሮች ፊት ለፊት እንደቆማችሁ አስቡ የኢያሱ ህጉን በድንጋይ ላይ መፃፍ እና ለህዝቡ ማንበብ ምን ያህል ትኩረት የሚስብ ነገር ነው?

______________________________________________________________________

ህጉ ሲነበብ በአእምሮአችሁ ውስጥ የሚመላለሰው ነገር ምንድነው?______________________

ያሉት በበረሀ ውስጥ ነው ፡፡ባይደክማቸው እና ግለቱ ባይፈጃቸው እንኳን ከፍተኛ ወበቁ ይሰማቸዋል፡፡ነገር ግን ሁሉም ሰው ሁሉንም ነገር ሰምቷል! በቁጥር 35 ላይ የተሰበሰበው ህዝብ በሙሉ ወንዶች፣ሴቶች፣ህፃናት እንዲሁም በመካከላቸው የሚኖሩ መፃተኞች በሙሉ የሙሴን ህግ ሲነበብ ሰምተዋል፡፡ እንደገናም ኢያሱ ሙሴ ያዘዘውን በሙሉ ነው ያደረገው፡፡ዘዳግም 31፡11-13 ያለውን ክፍል ተመልከቱ፡፡የህጉን ቃል ማንበብ ይህን ያክል አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው ?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ትግበራ፡**

የእስራኤል ህዝብ በሙሉ የህጉን መፅሐፍ እንዲሁም የምድሪቱን ህግ መስማት ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ተራሮችም እስራኤላውያን ህጉን ለመስማታቸው በመታዘዛቸው ስለሚያገኙት በረከት እንዲሁም አለመታዘዛቸው የሚያመጣባቸውን ውጤት እንዲያስቡ ምስክሮች እና መታሰቢያዎች ናቸው፡፡ህዝቡ በመታዘዝ የሚኖረው ህይወት እግዚአብሄር አምላካቸውን መውደዳቸውን እና ማክበራቸውን ያሳያል፡፡

አስቲ እናንተም ለእግዚአብሄር ቃል የምትሰጡትን ትኩረት ተመልከቱ። በምትኖሩበት አካባቢ ያሉ ተራሮች እና ኮረብቶች እናንተ ለእግዚአብሄር ቃል ስላላችሁ ስፍራ የሚመሰክሩ

ቢሆን ስለ እናንተ ምን የሚመሰክሩ ይመስላችኋል?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ከእግዚአብሄር ጋር ስላላችሁ ግንኙነት የሚመሰክሩ ንግግሮች ወይንም የአኗኗር ሁኔታዎች ምንድናቸው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ህይወታችሁ ስላመናችሁበት ነገር ምስክርነት ይሰጣል?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ህይወታችሁ እውነተኛ እንዲሆን እግዚአብሄር እንዲረዳችሁ የምትፈልጉበት አቅጣጫ ምንድነው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

**የምናሰላስለው፡**

መዝሙረ ዳዊት 1 ላይ በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ስላለ ተድላ እና ቃሉ የህይወታችን ማእከል እንደሆነ ይናገራል።ከዚህ በፊት አድርጋችሁት የማታውቁ ከሆነ እስቲ አሁን ግዜ ወስዳችሁ ይህንን ክፍል በማሰላሰል በአእምሮአችሁ ያዙት።እነዚህ ስድስት ቁጥሮች ብዙ ስእላዊ ቋንቋዎችን የያዙ ናቸው።እነዚህን ቁጥሮች በካርዳችሁ ላይ መያዝ አትዘንጉ።ይህን ክፍል ስታሰላስሉ የእግዚአብሄር ቃል ተድላ የሆነላቸው ሰዎች እንዴት አይነት የበረከት ህይወት

እንደሚኖሩ ልብ በሉ በቀጣዮቹም ቀናቶች ጥበቃው ሁልግዜ በእናንተ ላይ ከሆነው ከእግዚአብሄር ጋር ስላላችሁ ግንኙነት የተማራችሁትን ነገር ማስታወሻ ያዙ፡፡

**ፀሎት፡**

ጌታ ሆይ ቃልህ ተድላ እንደሆነላቸው እንዲሁም ቃልህን ለልጆቻቸው እንደሚያስተምሩት እንደ ኢያሱ እና እንደ እስራኤል ህዝብ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ካንተ ጋር ያለኝ ግንኙነት የሚታይ እና ሌሎችን ወደ አንተን ወደማወቅ በመምጣት አንተን አምላካቸው እራሳቸውን ደግሞ ያንተ እንደሆኑ መቁጠር እንዲችሉ የሚያደርግ ይሁን፡፡ ከአንተ ጋር ተስማምቼ እንድኖር የሚያደርገኝን ህግህን ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ ከዚህ በፊት ቃልህን እንደሚገባ ባለመታዘዜ ይቅር በለኝ፡፡ ይቅር ስላልከኝ፣ ስለማትጥለኝ፣ስለማትተወኝ አመሰግንሀለሁ፡፡አምላኬ ስለሆንክ ፣ልጅህ ስላደረከኝ ፣አዲስ ጅማሬንም ስለሰጠኸኝ አመሰግንሀለሁ፡፡

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

## <u>ትምህትርት ሶስት -ክፍል 2</u>

***መግቢያ፡***

በኢያሪኮ አና በጋይ የተደረገው ጦርነት በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ይህ ጦርነት እግዚአብሄር ገና ባልተወረሱት ምድሮች ውስጥ ባሉት ነገስታት ዘንድ እንዲፈራ አድርጎታል፡፡በኢያሱ 9፡1-2 ባለው ክፍል ላይ እንደምንመለከተው አንዳንድ ነስታት እስራኤልን ለመውጋት ጥምር ጦር መስርተዋል፡፡ በኢያሱ 9 ላይ ደግሞ የገባኦን ሰዎች እስራኤልን ለማታለል ተዘጋጅተዋል፡፡ እስራኤል የአህዛብ ነገስታትን በሙሉ ከምድሪቱ ላይ እየጠረገች ልትወርስ እንደሆነ ወሬው በአህዛብ መካከል እየተዛመተ ነው፡፡ህዝቡም ሁሉ ለህይወቱ ፈርቶ ነው ያለው፡፡

በዚህ የትምህርት ክፍል ብዙ ምዕራፎችን እንመለከታለን፡፡እነዚህ ምዕራፎች የጦርነት ታሪኮችን ናቸው፡፡እግዚአብሄር  ሙሴን ፣ሙሴ ደግሞ ኢያሱን እንዳዘዘው ኢያሱ እስራኤልን እየመራ አንድኛውን ግዛት ከአንዱ ቀጥሎ እያሸነፈ ምድሪቱን መቆጣጠሩን ቀጥሏል፡፡

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 9-11 አንብቡ፡፡እነዚህ ሶስት ምዕራፎች ስታነቡ የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በሉ፡፡

- ደጋግመው የተጠቀሱ ቃላት እና ሀረጎች ላይ አስምሩባቸው፡፡
- እግዚአብሄር ለእስራኤላውያን ምድራቸውን ያወረሰበትን መንገድ ለዩ፡፡

***መልመጃ፡***

1. እነዚህን የተደጋገሙ ቃላት እና ሃረጎች አገኛችኂቸው? ምን አይነት መልእክት ነው የሚስተላልፉት ?

ሀ. “አትፍሩ”__________________________________________

ለ. “የሚተርፍ አይኑር”_____________________________________

ሐ. “ሙሉ በሙሉ አጥፉ”___________________________________

2. እግዚአብሄር ለማሸነፍ የተጠቀመበት ያልተለመደ መንገድ ምንድነው ?

ሀ. ኢያሱ 10፡11________________________________________

ለ. ኢያሱ 10፡12-14______________________________________

ሐ. ኢያሱ 11፡20________________________________________

3. በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ገባኦናውያን እስራኤልን ሊያታልሉ ተዘጋጅተዋል፡፡ሌሎች ነገስታቶች እስራኤልን ለመውጋት ጥምር ጦር ሲያዘጋጁ ገባኦናውያን ምን ለማድረግ ነበር የወሰኑት?

__________________________________________________

የእቅዳቸው ፍፃሜ ምን ሆነ (ኢያሱ 9፡26-27) ?

__________________________________________________

__________________________________________________

እስራኤላውያን ከገባኦናውያን ጋር መሃላ በማድረጋቸው ምክንያት ከእነርሱ ጋር በመሆን አምስት የአሞራውያንን ነገስታት ወጉ፡፡ ኢያሱም ምርጥ የተባለውን ጦር በሚያስደንቅ ሁኔታ ሳከላቸው፡፡

- እግዚአብሄር በኢያሱ ተጠቅሞ ምን ሰራ?
    - ቁጥር 8_____________________________________
    - ቁጥር 10____________________________________

- ቁጥር 11____________________________________________
- ቁጥር 12-13____________________________________________

  - በቁጥር 14 ላይ የተገለፀው ምን ነበር?

    ________________________________________________

  - በቁጥር 16-27 ባለው ክፍል አምስቱ ነገስታት ምን ሆኑ?

    ________________________________________________

    ________________________________________________

    ________________________________________________

4. ኢያሱ 10፡28 እስከ ምዕራፍ 11 ድረስ የሚዘልቀውን ንግግር ይጀምራል፡፡ኢያሱ ምንም ነገር እንዳላስቀረ ሁሉንም እንዳጠፋ ይነግረናል እስራኤልን እየመራ ውጊያው ከአንድ ከተማ ወደሌላው ቀጥሏል፡፡ነገር ግን በዚህ ክፍል ውስጥ የእስራኤል መሪ ማን እንሆነ የሚያስታውሱንን ቃላትን ለማየት አልሞከርንም፡፡

ሀ. ኢያሱ 10፡30____________________________________________

ለ. ቁጥር 32______________________________________________

ሐ. ቁጥር 42_____________________________________________

የእስራኤል አምላክ ለእስራኤላውያን እየተዋጋ እንደሆነ ማወቅ ያስደስታል፡፡ የሚያሸንፍላቸው እርሱ ነው፡፡እስቲ ኢያሱ 10፡8 አስታውሱ፡፡እግዚአብሄር ኢያሱ እንዲያውቀው የፈለገው ነገር ምንድነው?

__________________________________________________

__________________________________________________

በቁጥር 25 ላይ ኢያሱ ለህዝቡ የነራቸው ምንድነው ?

________________________________________________

________________________________________________

መ. ምዕራፍ 11 ተመልከቱ ......የጠላት ጦር እንደ ባሕር አሸዋ በዝቶ ሲመጣ በቁጥር 6 ላይ እግዚአብሄር ለኢያሱ የነገረው ምንድነው?

________________________________________________

________________________________________________

5. ስለ ኢያሱ የተነገረን ምንድነው?

ሀ. ኢያሱ 10፡40________________________________________

ለ. ኢያሱ 11፡15________________________________________

ሐ. ኢያሱ 11፡23________________________________________

6. በመጨረሻ ኢያሱ 11 እንዲህ በሚል ቃል ይጠቃለላል፡

________________________________________________

**<u>ትምህርት ሶስት-ክፍል 3</u>**

**ትምህርት፡**

ባጠናቀቅነው መልመጃ ውስጥ ስለታሪክ እውነታ ተምረናል፡፡እስራኤላውያን በሚወርሷቸው ምድሮች ሁሉ በዚያ ምድር ከሚኖሩ ነገስታት ጋር ስለአደረጓቸው ጦርነቶች ተመልክተናለል፡፡እስራኤላውያን የኢያሱን ምሪት እስከተከተሉ ድረስ ድል እንደሚያገኙ ተመልክተናል፡፡ምድሪቱ በእግዚአብሄር በተሸነፉ ሰዎች ደም እርሳለች፡፡ለየትኞቹም ነገስታት ምህረት የለውም፡፡ነገር ግን ይህ ሁሉ ደም ማፍሰስ ያስፈልግ ነበር? እነዚህ ሰዎች ለእስራኤል ባሪያ ሆነው መኖር አይችሉም ነበር? የግድ መሞት ነበረባቸው?

እግዚአብሄር በጣኦት አምልኮ እና በኃጢአት የረከሰችውን ምድር የሚያፀዳው በደማቸው እንደነበር ማስታወስ ይኖርብናል፡፡የእስራኤል አምላክ እግዚአብሄር እንደሌሎቹ አማልክቶች ከእንጨት ወይንም ከድንጋይ የተሰራ አይደለም፡፡አምላካቸው እንዲሆን እና እንዲያመልኩት ከህዝቡ ጋር ቃል ኪዳን የገባ አምላክ ነው፡፡የእግዚአብሄር ህዝብ ያለመታዘዝ ዝንባሌ ያላቸው ፣አጉረምራሚዎች፣የማይረኩ እንዲሁም የራሳቸውን መንገድ ለመከተል የሚፈልጉ መሆናቸውን ስለሚያው ህዝቡን ወደዚህ እንደዚህ አይነት የአመፅ መንገድ ሊመሩ የሚችሉትን ነገሮች በሙሉ ማስወገድ ይፈልጋል፡፡የእግዚአብሄር ቅድስና ከእርሱ ጋር ቃኪዳን የሌላቸው ህዝቦች በሙሉ ያለርህራሄ እንዲጠፉ ይፈልጋል፡፡ቅድስናው ምድሪቱ እንድትነፃ እና እንድትቀደስ ይፈልጋል፡፡ህዝቡን የጠራቸው ለቅድስና ነው፡፡በፊቱም ነውር አልባ እንዲሆኑ ይፈልጋል (ዘዳግም 18፡9-13)፡፡

**ገለፃ፡**

እስቲ ጥቂት ግዜ ወስደን ስለ ቅድስናን እናውራ፡፡እነዚህነ የገለፃ ጥያቄ ልብ በሉ ወደልባችሁ የሚመጡትን መረዳቶች ደግም በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው፡፡

- ቅዱስ እና ያለነቀፋ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?
- መቀደስ ይቻላል? አንድ ሰው እንዴት ነው ቅዱስ መሆን የሚችለው?

- አንድን ሰው ቅዱስ ለማድረግ የግድ ደም መፍሰስ አለበት ወይንስ ሌላ አማራጭ ይኖራል?

- እኔ በእግዚአብሄር ፊት ያለነቀፋ ነኝ ማለት ምን ማለት ነው?

- በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ብዙ ደም ፈሷል፡፡እንስሳትን ይሰዉ ነበር ፣በጦርነት ይድገሉ እንዲሁም ይሞቱ ነበር፡፡ በየትኛው ስፍራ ላይ ነው ደም ከህይወት ጋር ግንኙነት የሚኖረው? ኢየሱስ ስለእኔ አለመቀደስ ፣ስለእኔ ኃጢአት እንደሞተልኝ አምናለሁ? በመስቀል ላይ ስለእኔ ያፈሰሰው ደም እኔን በሰማዮ አባቴ ፊት ቅዱስ ሊያደርገኝ ብቃት እንዳለውስ አምናለሁ?

**ፀሎት፡**

እግዚአብሄር አምላኬ ሆይ፣ በመስቀል ላይ በፈሰሰው በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ምክንያት ቅዱስ ስላደረከኝ አመሰግናለሁ፡፡እኔን ስትመለከት ሁለንተናዮን የሸፈነውን እና በፊትህ ያለነቀፋ ያደረገኝን የልጅህን ደም ነው የምትመለከተው፡፡የማይገባኝን በማድረግ ምህረትህን በእኔ ላይ አድርገሀል፡፡ኢየሱስ የእኔ ጀግና ነው፡፡ኢየሱስ ከአንተ ጋር የዘላለም ህይወት ሰጥቶኛል፡፡በእኔ ምትክ መስዋእት ስለሆነልኝ አመሰግንሀለሁ፡፡

**<u>ትምህርት ሶስት -ክፍል 4</u>**

ኢያሱ 11 እንዲህ በሚል ቃል ይጠቃለላል "ምድሪቱም ከጦርነት አረፈች" ጦርነት ፣ጦርነት፣ጦርነት !እስራኤላውያን እግራቸው ምድሪቱን ከረገጠበት ወቅት ጀምሮ ጦርነት አላቋረጠም ነበር እያንዳንዱን ምድር ሲያስለቅቁ ጦርነት ነበር፡፡በኢያሱ 12 ላይ እስራኤላውያን ድል ያደረጓቸው 31 ነገስታት በሙሉ ተዘርዝረዋል፡፡ምዕራፍ 13 እግዚአብሄር ባለፉት አመታት ብዙ ልምድ ላካበተው ኢያሱ "ገና ያልተወረሰ ብዙ ምድር እንዳለ ሲነግረው ያሳየናል ቁጥር 1-7 ባለው ክፍል ውስጥ ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች እንማራለን፡፡

- የቀረው ምን አይነት ምድር ነው?(ቁጥር 2-5)
- እግዚአብሄር ምን ሊያደርግ ነው ቁጥር 6
- ኢያሱስ ምን ሊያደርግ ነው?

ቁጥር 32 ላይ ሙሴ ለሶስት ነገዶች ማለትም ለጋድ፣ለሮቤል እና ለምናሴ ነገድ በከፊል ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ ያለውን ምድር ቃል ገብቶላቸዋል ምድሪቱም በቁጥጥር ስር ውላለች፡፡በኢያሱ 13፡8-32 እነዚህ ሶስት ነገዶች የተከፋፈሏቸው ምድሮች ድንበር ተገልፆልናል፡፡

በኢያሱ 14 ላይም ከዮርዳኖስ ምዕራብ በኩል ያለውን ምድር ለቀሪዎቹ ነገዶች እንዴት እንደተከፋፈለ እዲሁም ለካሌብ እና ለሌሎቹ ሰላዮች ስለተሰጣቸው እርስት እንመለከታለን፡፡እንደገና በቁጥር 14፡23-25 ላይ "ምድሪቱም ከጦርት አረፈች የሚል ቃል ተፅፎ እናገኛለን፡፡

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 15-21 ያለው ክፍል የትኛው መሬት ለማን እንደተሰጠ ይነግረናል፡፡ ከአስራሁለቱ ነገዶች ውስጥ ርስት ያልተሰጠው ለሌዊ ነገድ ብቻ ነው፡፡ ኢያሱ 13፡33 የሌዊ ነገድ ርስት ምን እንደሆነ ይነግረናል ?

ዘኑልቁ 18፡20-21 ተጨማሪ መረጃ ይሰጠናል፡፡እግዚአብሄር እንዴት ነው አቅርቦቱን የሚያዘጋጅላቸው?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

ኢያሱ 21፡43-45 ያለውን ክፍል አንብቡ፡

- እግዚአብሄር ለእስራኤል ______________________________________ሰጠ
- እግዚአብሄር_______________________________________________ሰጠ
- እግዚአብሄር________________________________________ ብሎ ቃል ገባ

እግዚአብሄር አደርጋለሁ ብሎ የተናገረውን ነገር በሙሉ አደረገ፡፡በእነዚህ ሁሉ አመታት ውስጥ በህዝቡ መካከል የገለጠው ታማኝነት ከማረጋገጫ በላይ ነው፡፡ምድሪቱን የወረሱት ይህን ተስፋ ቃል የተቀበሉት ሰይሆኑ ልጆቻቸው ናቸው፡፡

**መልመጃ፡**

እስራኤልን አሁን ወዳሉበት ደረጃ ያመጣቸውን ታሪኮች እና ልምምዶች ልብ በሏቸው፡፡በዘመናት ሁሉ እግዚአብሄር የተናገረውን የተስፋ ቃል ያስባል፡፡እነርሱም ልጆቻቸው እንጂ እነርሱ ምድሪቱን እንደማይወርሱ ያውቃሉ፡፡የእግዚአብሄር የተስፋው ፍፃሜ የሚያርፈው በቃሉ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ከህዝቡ ጋር ያደረገው ቃልኪዳን ይህ ነበር፡፡እግዚአብሄር ለአብርሀም እና ለዘሩ የገባው የተስፋ ቃል የሚመሰረተው እግዚአብሄር ቃሉን ለመፈፀም ባለው ታማኝነት ላይ ነው ዘፍጥረት 17፡7 ፡፡ እስቲ አስካሁን የተመለከትናቸውን የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በክለሳ መልክ እንደገና በማንበብ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው፡፡ለእናንተ በጣም አስፈላጊ ናቸው የምትሏቸውን ታሪኮች በተለየ መልኩ ፃፏቸው ለእናንተም ለምን በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ አስቡ፡፡

ጥናታችንን ከመቀጠላችን በፊት በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የሚገኙትን ሶስት የተለያዩ ጥቅሶች አንመልከት፡፡

1. ኢያሱ 13፡13____________________________________________

2. ኢያሱ 15፡63____________________________________________

3. ኢያሱ 16፡10____________________________________________

እነዚህ ጥቅሶች በጥልቀት ልናጠናቸው ሳይሆን የኢያሱን መፅሐፍ ጨርሰን የመሳፍንትን መፅሐፍ ልንጀምር መሆናችንን እንድትረዱ ለማድረግ ያክል እነዚህን የኢያሱ መፅሐፍ መደምደሚያ የሆኑትን ክፍሎች ማየት አስፈልጎናል፡፡

**የቤት ስራ፡**

ኢያሱ 23 አንብባችሁ ኢያሱ ህዝቡን ፣ ሽማግሌዎቻቸውን ፣ መሪዎቻቸውን ፣ፈራጆቻቸውን ፣ እንዲሁም የተለያየ አገልግሎት የሚያገለግሉትን ሁሉ ጠርቶ ያደረገውን የስንብት ንግግር ይዘት አስቡ፡፡

- ያላለቀው ስራ ምን ነበር?
- የሙሴም ህግ በተመለከተ የተናገረው ማበረታቻ ምን ነበር?
- በረከቶቹ ምን ነበሩ?
- እርግማኖቹስ ምን ነበሩ?

**<u>ትምህርት ሶስት-ክፍል 5</u>**

***መልመጃ፡***

1. የቀረው ስራ ምን ነበር (ኢያሱ 23፡3-5)

2. የኢያሱ ትእዛዝ ምን ነበር (ቁጥር 6-8)

በቁጥር 7 መሰረት እስራኤላውያን ሊታዘዟቸው የሚገባአው አራት ነገሮችን ነው፡፡

- __________________________________________________
- __________________________________________________
- __________________________________________________
- __________________________________________________

3. ቢታዘዙ በረከታቸው ምን ነበር (ቁጥር 9-11)?

__________________________________________________

__________________________________________________

4. ያለ መታዘዛቸውስ ውጤት ምን ነበር(ቁጥር 12-16)

__________________________________________________

__________________________________________________

5. በማጠቃለያውን ኢያሱ ስለእግዚአብሄር ታማኝነት አስታወሳቸው፡፡ እስራኤላውያንን ወደምን ነበር የጠራቸው ?

__________________________________________________

__________________________________________________

__________________________________________________

**የቤት ስራ፡**

*መፅሐፈ* ኢያሱ 24 አንብቡ፡፡

**ክለሳ፡**

1. ኢያሱ ጥቂት የእስራኤልን ታሪክ በክለሳ መልክ ተናገረ፡፡ እስቲ ታሪኮቹን ፣ ህዝቦቹን ፣ እግዚአብሄር በሁሉም ጆሮዎች እንዲሰማ አደረገ ፡፡

ሀ. ቁጥር 2-4 የዘፍጥረት ታሪኮችን ተናገረ፡፡

ለ. ቁጥር 5-7 ዘፀአት ውስጥ ስላሉ ታሪኮች ተናገረ፡፡

ሐ. ቁጥር 8-10 እስራኤላውያን በዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ስለነበራቸው ልምምድ ተናገረ፡፡

መ. ቁጥር 11-13 እስራኤላውያን ምድሪቱን ስለመቆጣጠራቸው ተናገረ፡፡

እነዚህ ሁሉ ታሪኮች የእስራኤል ታሪኮች ናቸው፡፡በእነዚህ ሁሉ ታሪኮች ውስጥ ዋናው ባለታሪክ እግዚአብሄር ነው፡፡ እግዚአብሄር ለአብርሀም ________________ ሰጠ፣ሙሴ እና አሮንን ________________ላከ፣እስራኤልን ከ________________አወጣ፣እግዚአብሄር ብዙ ህዝቦችን እና ምድራቸውን በእጃችሁ አሳልፎ ሰጣችሁ________________ቁጥር 13 ምን ይላል ?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2. ኢያሱም እግዚአብሄር ያደረገውን በሙሉ በፊታቸው ተናገረ እነሱም በህዝቡ ሁሉ ፊት እንዲያውጁት አደረገ (ቁጥር 14)፡፡በ መፅሐፈ ኢያሱ 24፡15 ላያ ኢያሱ የጠየቃቸው ምን ነበር?

________________________________________________________________

በቁጥር 15 ላይ ኢያሱ የገለፀው ነገር ምን ነበር ?

________________________________________________________________

በቁጥር 21 ላይስ ህዝቡ የተናገረው ምን ነበር ?

______________________________________________________________

ህዝቡም እግዚአብሄርን ለማገልገል እና ለመታዘዝ አንዱ ለአንዱ ምስክርነት እማኝ በመሆን ምስክርነታቸውን ሰጡ፡፡ እንደ ማህበር መዝገብ ሊኖራቸው መዝገቡንም ሀሉም እንዲጠብቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡ይህም ማለት በቁጥር 23 ይህ ህዝብ________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

_____ማድረግ አለበት፡፡

3. ኢያሱ ሞተ፡፡ በቁጥር 31 ላይ እራኤል እንዳገለገለ ተነግሮናል፡፡እግዚአብሄርን ለምን ያህል ግዜ እንዳገለገሉት ነው የምናውቀው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

በመጨረሻ አስራኤላውያን ወደ ከነአን ገቡ፡፡እግዚአብሄር በምድረበዳ ውስጥ ሲቅበዘበዙ ታማኝ በሆነ መገኘቱ በመርዳት ከእረጅም ጊዜ በፊት የገባውን ተስፋ በመፈፀም የተስፋይቱን ምድር አወረሳቸው፡፡ ምድሪቱ የእነርሱ ንብረት ሆናለች፡፡ነገሮች አሁን ይለያሉ ሁሉም ነገድ ወደየእርስቱ ሲሄድ የህዝቡ ህይወት ከቀድሞው የተለየ ይሆናል፡፡ መሪዎቻቸው እየሞቱ ነው፡፡እንግዶች እና ሌሎች ህዝቦች በመካከላቸው እየኖሩ ነው እነዚህ እንግዳ ህዝቦች ፈፅሞ መጥፋት አለባቸው፡፡በትምህርት 4 ኢያሱ የመጨረሻውን ንግግር ሲያደርግ እንሰማዋለን፡፡

**ትምህርት አራት-ክፍል 1**

**ገለፃ፡**

አሁም ወደ ኢያሱ የህይወት መጨረሻ መጥተናል፡፡እስራኤላውያን ወደየ ርስታቸው ተበትነዋል ሁሉም በአዲሱ ምድር አዲስ ህይወት ጀምረዋል፡፡ኢያሱ 110 አመት ኖሮ ሞተ፡፡ ከካሌብ በስተቀት ከሌሎቹ እስራኤላውያን የበለጠ የህይወት ልምድ ያለው ሰው ነበር፡፡

የኢያሱ ስንብት ሙሴ ከመሞቱ በፊት ህዝቡን የተሰናበተውን ሰንብት ያስታውሰናል፡፡ በረከቶቹ እና መርገሞቹ ግን አሁንም አሉ፡፡ህዝቡ መታዘዝን ከመረጠ ይባረካል፡፡የመረጡት አለመታዘዝን ከሆነ ደግሞ እርግማን ያገኛቸዋል፡፡ኢያሱ የህዝቡን ልብ ስለሚያውቅ ይህን ነገር እንዲያስታውሱ አደረጋቸው፡፡በሲና ተራራ ከነበራቸው ማንነት የተነሳ ጣኦታትን ሊያመልኩ እንደሚችሉ ያውቅ ነበር፡፡ምንም እንኳን እግዚአብሄር ለእነሱ መልካም ቢሆንም ካለ መታዘዛቸው የተነሳ ብዙ ግዜ ከባድ ጥፋትን በመካከላቸው አምጥቶባቸዋል (ኢያሱ 24፡20)

ምናልባት ልጆች ከሆናችሁ አያቶቻችሁ ስለዚህ ታሪክ ለምን እንደሚነግሯችሁ ላትረዱ ትችላላችሁ፡፡ምክንያታቸው በህይወታቸው ብዙ ስለተማሩ ነው፡፡እነሱን ለሚከተላቸው የሚናገሩት ጥበብ አላቸው፡፡እስቲ አንድ የእድሜ ባለጠጋ የነገራችሁ የምታስታውሱት ነገር ይኖራችኋል?

________________________________________

________________________________________

የሚያካፍሏችሁ ጥበብ ለእናንተ በረከት ነው፡፡ አስታውሳለሁ ብላችሁ የተናገራችሁበትን ወቅት ትዝ ይላችኋል ? ያለፈውን ነገር ማስታወስ ያለፈውን ስህተታችንን ከመድገም ይጠብቀናል፡፡ የምታስታውሷቸው የሚያበረታቷችሁ ነገሮች ምንድናቸው ?

________________________________________

________________________________________

እሰቲ አሁን ወደ እድሜያችሁ ማብቂያ እንደመጣችሁ አስቡ፡፡በህይወት ልምዳችሁ ያገኛችሁት ሰዎች እንዲያስታውሱት የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?

---

---

**የምናሰላስለው፡**

በኢያሱ 24፡15 ላይ ያለው ክፍል እንዲህ ይላል "እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለ!"

**ፀሎት፡**

በሀወይወቴ ዘመን ሁሉ እንደ ኢያሱ በድፍረት አቋም ይዤ አንተን ማገልገል እፈልጋለሁ፡፡አንተ ለእኔ ታማኝ ነህ ፡፡እኔም አንተን በታማኝነት እንዳገለግልህ አድርገኝ፡፡በዚህ ዓለም ያሉ ነገሮች ብዙ መልካም የነገር አማራጮችን ታቀርባለች፡፡ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ካንተ ሊያርቁኝ የሚችሉ እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡አንተን እና አንተን ብቻ ለማገልገል ያለኝ ቁርጠኝነት እስከመጨረሻው ይፀና ዘንድ እርዳኝ፡፡በተለይ በልቤ ፈተና በሆኑብኝ ነገሮች ላይ እርዳኝ፡፡

---

---

---

---

**መግቢያ፡**

ኢያሱ ሞቷል፡፡ አሁን መሪ የላቸውም ፣የሚተካም የለም ፡፡የእስራኤል የታሪክ ምዕራፍ ተፈፀመ፡፡ ከግብፅ ነፃ መወጣት፣ለአርባ አመት የምድረበዳ ጉዞ፣ከዚያም የተስፋይቱን ምድር

መውረስ በስኬት ተጠናቀዋል፡፡ሁሉም ነገዶች ድርሻ ድርሻቸውን ወስደዋል፡፡ምድሪቱም ከጦርነት አርፋለች፡፡

አሁን መሪ ያስፈልጋቸው ይሆን? የጉዞው ነገር አሁን አክትሟል ወደ ሚሄዱበት ደርሰዋል፡፡ ስለዚህ ቀጥሎ የሚሆነው ምንድነው? እስከዛሬ የኖሩት ኑሮ ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ እየተዘዋወሩ ነው አሁን ግን ተረጋግተው የሚኖሩበትን ርስታቸውን ወርሰዋል፡፡ከዚህ በኋላ በመሪ ላይ ተደግፈው አይኖሩም፡፡አሁን ብዙ ሆነው አይጓዙም ነገር ግን ለየነገዱ ወደተሰጠው ርስት ሄደው ተራርቀው ነው የሚኖሩት፡፡

በተመሳሳይ መልኩ እግዚአብሄር እነሱን እንደ አንድ ህዝብ የሚፈልጋቸው የቃኪዳን ህዝቦች እንደሆኑ እናስታውሳለን፡፡ ሙሴም ሆነ ኢያሱ የበረከት ህይወት መኖር ከፈለጉ በመታዘዝ መኖር እንዳለባቸው አስታውሰዋቸዋል፡፡ህዝቡም የእግዚአብሄርን ህግ አለመታዘዛቸው እና ሌሎች አማልክቶችን ማምለምክ የሚስከትልባቸው እርግማን ምን እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ህጉ የተሰጣቸው የእግዚአብሄር ህዝብ ሆነው እንዲኖሩ እንዲሁም በሚቀመጡበት ምድር ሁሉ ተፈገፃሚ እንዲያደርጉት እንዲጠብቁት እግዚአብሄር ይፈልጋል፡፡

አሁን የመሳፍንትን መፅሐፍ ማጥናት ልንጀምር ነው፡፡ መሪ የሌላቸው ነገር ግን ገና ያልተወረሰ ብዙ ምድር ያላቸው እስራኤላውያን ምን ገጥሟቸው ይሆን?

**<u>ትምህርት አራት-ክፍል 2</u>**

**የቤት ስራ፡**

*መሳፍንት 1፡19-36 ያለውን ክፍል እንብቡ፡፡*

**መልመጃ፡**

የእግዚአብሄር ትእዛዝ በምድሪቱ ላይ ያሉ ህዝቦች በሙሉ እንዲጠፉ ነው፡፡ምን አይነት ሰው እንዲተርፍ አልፈቀደም፡፡እስራኤላውያን በምድሪቱ ላይ ካሉ ሰዎች ጋር ምን እንዳደረጉ የሚገልፁትን በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ ያሉትን ሀረጎች አስምሩባቸው፡፡

| ጥቅሶች | እስራኤላውያን በምድሪቱ ላይ ከሚኖሩት ጋር ምን አደረጉ |
|---|---|
| መሳፍንት1፡19 | |
| መሳፍንት1፡21 | |
| መሳፍንት1፡25 | |
| መሳፍንት1፡27 | |
| መሳፍንት1፡28 | |
| መሳፍንት1፡29፣30፣31፣33 | |
| መሳፍንት1፡34 | |

እስራኤላውያን ጠላቶቻቸውን ከማስወገድ ይልቅ በምድሪቱ ላይ እንዲኖሩ ፈቀዱላቸው፡፡ በራሳቸው መንገድ በመሄድ የአግዚብሄርን ትእዛዝ ቸል አሉ፡፡ ለነገዳቸው ስፍራ አግኝተዋል ፡፡ በጣም ደስተኛ እና የረኩ ህዝቦች ሆነዋል በምድሪቱ ላይ እንዲኖሩ የፈቀዱላቸውንም ሰዎች

ባሪያዎች አድርገዋቸዋል።ታዲያ የሰዎቹ በዚያ ምድር መኖር ምን ያስገርማል? አብረው በሰላም መኖር አይችሉም?

**የቤት ስራ፡**

መሳፍንት 2፡1-5 አንብቡ።

**መልመጃ፡**

- የጌታ መልአክ ምን እንዳደረገ ነው የነገራቸው (ቁጥር 1)?

  ______________________________

  ______________________________

- ምን ሊያደርጉ ነው (ቁጥር 2) ?

  ______________________________

  ______________________________

- ምን ነበር ያደረጉት?

  ______________________________

  ______________________________

- ያስከተለው ምን ነበር (ቁጥር 3)?

  ______________________________

  ______________________________

- የህዝቡ ምላሽ ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 4-5)?

  ______________________________

እነዚህ ጥቅሶች እንደ ወረርሽኝ የሆነውን የእስራኤልን ችግር ምንጭ የሚገልፁ ናቸው።የምድሪቱ ባለቤት የመሆን መብታቸውን አሳልፈው ሰጡ።የቀረው የምዕራፍ ሁለት ክፍል ኢያሱ ከሞተ በኋላ በአስራኤላውያን ዘንድ ምን እንደተፈጠረ አጠቃሎ ይገልፅልናል።

**የቤት ስራ፡**

*መሳፍንት* 2፡6-23 *ያለውን ክፍል አንብባችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ*

- እስራኤላውያን በኢያሱ የህይወት ዘመን ምን ነበር ያደረጉት?
- ቀጣዮስ ትውልድ በምን መልኩ ነበር የኖረው?
- የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበር?
- እግዚአብሄር ላስነሳላቸው መሳፍንት የእስራኤላውያን ምላሽ ምን ነበር?
- በህዝቡ ላይ የእግዚአብሄር እርግማን ምን ነበር?

***መልመጃ፡***

1. በኢያሱ የህይወት ዘመን እስራኤላውያን እንዴት ነበር የኖሩት (ቁጥር 6-7)

______________________________________________

______________________________________________

ይህ ወቅት የሰላም ወቅት ነው እግዚአብሄርን በማገልገለ እግዚአብሄር ያደረገላቸውን ብዙ ትልልቅ ነገሮች ተመልክተዋል፡፡አሁን ግን ኢያሱ ሞቷል፡፡

2. ነገር ግን የእስራኤል ታሪክ ወሳኝ ለውጥ ሲያደርግ እንመለከታለን፡፡በቁጥር 10 ላይ የተገለፀው ነገር ምንድነው?

______________________________________________

______________________________________________

ፈጣኑ ጥያቄ የሚሆነው ፡ቀጣዩ ትውልድ እግዚአብሄርን እንዲሁም እግዚአብሄር የሰራውን ያላወቀው ለምንድነው?

## ገለፃ

እንዴት ነው ነገሮችን በፍጥነት የምንረሳው! ሌሎች ካላሳሰቡን ወይንም ነገሮችን መለስ እያልን ካላስታወስናቸው በቀር መርሳታችን አይቀርም፡፡እናንተስ በዚህ ዙሪያ ያላችሁ ልምምድ ምንድነው?

- እግዚአብሄር የሰራውን ነገር ሌላ ሰው አስታውሷችሁ ያውቃል?እንደዚያ ያደረገው ሰው ማነው?

- ከእናንተ በፊት የነበረው ትውልድ እግዚአብሄርን ያውቅ ነበር? ስለዚያ ነገር ተነግሯችሁ ያውቃል?

ምን ነበር የተነገራችሁ?

ወይንም ደግሞ ስለእግዚአብሄር ምንም ተነግሯችሁ አያውቅ ይሆናል፣ በዚህ ምክንያት ስለ እግዚአብሄር ታላቅ ፍቅር ምንም አታውቁ ይሆናል ፡፡ታዲያ ከእግዚአብሄር ፍቅር ውጪ ምን አይነት ቋሚ ትዝታ ሊኖረን ይችላል?

**<u>ትምህርት አራት - ክፍል 3</u>**

**መልመጃ:**

1. መሳፍንት 2፡11-12 ያለው ክፍል እስራኤላውያን ምን እንደፈፀሙ ይነግረናል?

    - የእስራኤል ልጆች_____________________ አደረጉ_________________አመለኩ፡፡
    (በአሊም የአህዛብ አምላክ ነው)
    - _________________ያወጣቸውን _____________እግዚአብሔርን ተዉ፥
    - _______________አማልክት ተከተሉ፥_____________እግዚአብሔርንም አስቈጡ፡፡

2. ለዚህ ድርጊታቸው የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበር? (ቁጥር 12-16)

    - ____________________ የአባቶቻቸውን አምላክ እግዚአብሔርን _____________፥
    - ለምንድነው የተውት? በዙሪያቸውም ካሉት ከአሕዛብ __________________.፥ ሰገዱላቸውም እግዚአብሔርንም ___________፡፡እግዚአብሔርንም ትተው ____________እና ____________አመለኩ፡፡
    - እግዚአብሄር ምን አደረገ?
        - ቁጥር 14

        ______________________________________________________________________

        ______________________________________________________________________

        - ቁጥር 15

        ______________________________________________________________________

        ______________________________________________________________________

3. ቁጥር 16 እግዚአብሄር መሳፍንትን አስነሳ ?

______________________________________________

______________________________________________

*ማስታወሻ፡ መሳፍንት ወታደራዊ አይነት መሪዎች ሲሆኑ እግዚአብሄርም እስራኤላውያንን በዙሪያቸው ካሉ ጠላቶቻቸው ጥቃት ለመታደግ በተለያየ ወቅት ያስነሳቸው የተለያዩ ሰዎች ናቸው፡፡*

4. ታዲያ ህዝቡ እነዚህን መሳፍንት እንዴት ነበር የተቀበላቸው (ቁጥር 17)?

______________________________________________

______________________________________________

5. እግዚአብሄር ካስነሳቸው መሳፍንቶች ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

6. እግዚአብሄር ከህዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት ምን ሆነ (ቁጥር)?

______________________________________________

______________________________________________

7. እግዚአብሄር ምን ለማድረግ ወሰነ (ቁጥር 21-23) ?

______________________________________________

______________________________________________

**ገለፃ፡**

ጥሩ ገፅታ አይደለም፡፡ከዚህ ትውልድ በፊት የተገለጠው የእግዚአብሄር ታማኝነት በዚህ ትውልድ ተዘንግቷል፡፡በቃልኪዳኑ ላይ ማመፃቸው እንዲሁም አለመታዘዛቸው ከምድሪቱ ላይ መወገድ ሲገባቸው ያልተወገዱትን አህዛብ ከድንጋይ እና ከእንጨት ከተሰሩት አማልክት በአሊም ተብሎ ከሚጠራው የሴማውያን አምላክ እንደዚሁም (ዘርን የምትሰጥ ተባላ የምትታመነውን) አስታሮት ጋር እራሳቸውን ለምንዝርና አሳልፈው ሰጡ ፡፡ ከሚወዳቸው እና

ከሚያድናቸው አምላክ ፊታቸውን  አዙረው በባርነት እና ግዞት የሚገዟቸውን ባእዳን እና እንግዳ አማልክት አመለኩ።አያቶቻቸው በግብፅ የሚያውቁትን ግዞት እንዲገዟቸው ለአማልክቶቹ እራሳቸውን አሳልፈው ሰጡ።እነዚህ አማልክት በሰው ሃሳብ የተፈጠሩ ናቸው።ህይወትም ሆነ እስትንፋስ የሌላቸው፣ ዋጋ የሌላቸው፣ ሞትን የሚያመጡ አማልክት ናቸው።ሙሴ እና እያሱ እግዚአብሄርን እንዳይተዉ አስጠንቅቀዋቸዋል ህዝቡም በእራሳቸው አፍ "እግዚአብሄርን እናገለግላለን ብለው ተናግረዋል" (ኢያሱ 24፡21)ይሆን ቃልኪዳናቸውን ያስታውሱ ደግሞም ይጠብቁት ይሆን?

**ትግበራ፡**

የራሳችንን እንዲሁም የሌሎችን ህይወት ስንመለከት እራሳችንን እንዲህ ብለን እንጠይቃለን "ቃልኪዳናችንን እናስታውሳለን ወይንስ ዘንግተነዋል?"

1. እግዚአብሄር ካደረገልኝ ነገር የተማርኩት ነገር ምንድነው? እንደፈጠረኝ አስባለሁ? እንደጠራኝ፣ነፃ እንዳወጣኝ፣ እንደዋጀኝ፣ እንዲሁም ልጁ እንዳደረገኝ  አስታውሳለሁ? እርሱ አምላክ ሲሆነኝ እኔንም የእርሱ ልጅ እንዳደረገኝ አስታውሳለሁ? ሌላስ የማስታውሰው ነገር ምንድነው?

   __________________________________________________

   __________________________________________________

2. በፊቱ ቅዱስ እና ነውር አልባ እንድሆን እንደጠራኝ አስታውሳለሁ? በፈሰሰው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ቅዱስ እና ያለነቀፋ እንዳደረገኝ አስታውሳለሁ? በጥምቀት በውሃ ውስጥ በማለፌ ለራሴ ሞቼ ለርሱ ህያው መሆኔን እንዳወጅኩ አስታውሳለሁ? ሌላስ የማስታውሰው ምንድነው?

   __________________________________________________

   __________________________________________________

3. ከእኔ በኋላ ያሉትስ ማን እንደነበሩ ያስታውሱ ይሆን? ታሪካቸውን ያስታውሱ ይሆን? እግዚአብሄር ለእነሱ ያለውን ታላቅ  ፍቅር ያውቁ ይሆን? እግዚአብሄር ያደረገላቸውን

ነገር እንዳይረሱት መንገርን እና ማስታወስ ይኖርብኝ ይሆን? እንድነግራቸው ማስታወስ ያለብኝ ነገር ምንድነው?

______________________________________________________

______________________________________________________

**ፀሎት፡**

ጊዜ ወስዳችሁ እግዚአብሔር በልባችሁ እንዲሞላ እየጠየቃችሁት የራሳችሁን ፀሎት ፃፉ፡፡የእርሱን ታላቅ ፍቅር ላልሰሙት ሰዎች ያላችሁን ሸክም አካፍሉት፡፡ በውስጣችሁ የሚመጡትን ሰዎች ይዛችሁ የአግዚአብሄርን ፍቅር እንድትነግሯቸው ድፍረት እና ብርታት እንዲሰጣችሁ ጠይቁት፡፡

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

______________________________________________________

## ትምህርት አራት-ክፍል 4

**የቤት ስራ፡**

*መሳፍንት* 3፡1-5 *ያለውን ክፍል አንብቡ።ይህ ምእራፍ የጦርነት ልምድ የሌላቸውን እስራኤላውያንን ለማሰልጠን በምድሪቱ ላይ ስለተዋቸው ህዝቦችን ዝርዝር በመናገር ይጀምራል።እነዚህ ህዝቦች* __________________________, ____________________, __________________________, *እና* ______________________*ናቸው* (*ቁጥር* 3)

*በቁጥር* 4 *መሰረት እግዚአብሄር ለምን ሊፈትናቸው ፈለገ*?

____________________________________________________________

__________*እስራኤላውያን ምን በማድረግ ደመደሙ* (*ቁጥር* 5-6)

1. (*ቁጥር* 5) __________________________________________________
2. (*ቁጥር* 6) __________________________________________________
3. (*ቁጥር* 6) __________________________________________________

**መልመጃ፡**

*በመዝሙር* 106፡34-39 *መዝሙረኛው በዚያን ወቅት ስለነበረው የእስራኤልን ታሪክ ሁኔታ ማጠቃለያ ይሰጠናል።ይህም እንደቀደመው ክፍል ስለሁኔታው ጥሩ ምስል አይሰጠንም። እስራኤላውያን ስላደረጉት ምርጫ እነዚህ ስድስት ቁጥሮች የሚነግሩንን ነገር ከግንዛቤ ውስጥ አስገቡ ።*

1. *ቁጥር* 34-35 :*ያልታዘዙት በምን ነበር*?

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

በዚያ ፋንታ ምን መረጡ?

______________________________________________

______________________________________________

2. ጣኦት አምልኮአቸውስ?

ሀ. ቁጥር 36: ______________________________________

ለ. ቁጥር 37: ______________________________________

ሐ. ቁጥር 38: ______________________________________

3. ቁጥር 39፡ በሥራቸው ____________________፥ ____________________ አመነዘሩ።

**ትምህርት፡**

አንዱ መስፍን ከሌላው ቀጥሎ ሲነሳ የተለያየ አይነት የባህሪ ይገለጣል።በዚህ የጥናት ክፍል መሳፍንት 2፡16-19 ተመልክተናል።ኡደቱ ይህን ይመስላል።

እስራኤል ሌሎች አማልክቶችን በማምለክ ክፉ ነገርን አደረጉ

እግዚአብሄር እስራኤልን ወደንሰሃ የሚያመጡ መሳፍንትን አስነሳ (ንሰሃ)

እግዚአብሄር ከጠላቶቻቸው አዳናቸው(ማዳን)

እግዚአብሄር በፀጥታ እና በሰላም እንዲኖሩ አደረጋቸው (እረፍት)

ደግመው ደጋግመው እስራኤላውያን ከከቀድሞው በከፋ መንገድ ሄዱ።

እያንዳንዱን ምዕራፍ በዝርዝር ማየት ባንችልም ጥቂት መሳፍንትን በመመልከት የእስራኤላውያንን የባህሪ አይነት እንመለከታለን፡፡ህይወታቸውን ለእግዚአብሄር ባለመስጠት የተጓዙ ሰዎችን በትኩረት ለመመልከት ምልክት ማድረጊያ ማርከሮቻችሁን ያዙ፡፡

**መልመጃ:**

በመሳፍንት 3:7-11 ላይ ወዲያውኑ የባህሪ ንድፍ ተመሰረተ፡፡

- እስራኤላውያን ምን አደረጉ (ቁጥር 7) ?
  - ____________________
  - ____________________
  - ____________________

  እግዚአብሄርን ረስተው በሌላ አምላክ ተኩት

- ለባህሪያቸው እግዚአብሄር የሰጣቸው ምላሽ ምንድነው?
  - ____________________
  - ____________________

  እስራኤላውያ ለባእድ ነገስታት እንዲገዙ አደረጋቸው፡፡

- አስራኤላውያን ለግዞታቸው የሰጡት ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 9)?
  - ____________________

  ግዞቱ ሳይመቻቸው ሲቀር ወደ እግዚአብሄር ጮሁ፡፡

- እግዚአብሄር እንዴት ነበር የመለሰላቸው (ቁጥር 9)
  - ____________________

  እግዚአብሄር የሚያድናቸው መስፍን አስነሳላቸው፡፡

- መሳፍንት እስከነበሩበት ዘመን ድረስ________በምድሪቱ ላይ________ነበር፡፡(ቁጥር 11)

## ትምህርት አራት-ክፍል 5

### የቤት ስራ

መሳፍንት 3፡12-16፣30 እና መሳፍንት 4፡1 አንብቡ፡፡በጣም የሚያሳዝን ምስል ነው ፡፡ነገር ግን ቁጥር 12 "*እንደገና*" በሚል ቃል ይጀምራል፡፡

**መልመጃ፡**

የተለያየ ቀለም ባለው ማርከሮቻችሁ ስለእስራኤል የባህሪ ኡደት የሚናገሩትን የሚከተሉትን ክፍሎች አስምሩባቸው፡፡

1. እስራኤላውያን ምን አደረጉ?
2. የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበር?
3. እስራኤላውያን ምን ገጠማቸው?
4. እስራኤላውያን ምን አደረጉ ?
5. እግዚአብሄር ምን አደረገ?
6. የምድሪቱ አዲስ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?
7. መሳፍንቶቹ ምን ሆኑ? እናም "*እንደገና*"..........

ጎቶንያል፣ናኦድ፣ዲቦራ እንዲሁም ጌዲዮን መሳፍንት ነበሩ፡፡በመሳፍንት 8፡33-35 ውስጥ ስናነብ ብዙም ሳይቆይ ጌዲዮን ሞተ እስራኤላውያንም እንደገና በአልን በማምለክ አመነዘሩ፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ብለን ልንጠይቅ እንችላለን፡

- የአህዛብ አማልክት ምን የሚወደድ ነገር ኖሯቸው ነው እስራኤላውያን እነሱን በማምለክ ራሳቸውን የሚያረክሱት?

  ______________________________

- በዙሪያቸው ካሉ ጠላቶቻቸው በሙሉ ያዳናቸውን አምላካቸውን እግዚአብሄርን የተውት ለምንድነው (ቁጥር 34) ?

  ______________________________

  ______________________________

- ከተደረገላቸው መልካም ነገር የተነሳ  ለመሪዎቻቸው ርህራሄ ያጡት ለምንድነው (ቁጥር 35) ?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**መልመጃ:**

እስራኤላውያን የሚያደርጉትን ሁሉ እያደረጉ ያሉበትን ምክንያት አራት የተለያዩ ቃላት እና ሃረጎች ማጠቃለያ ሃሳብ ይሰጡናል፡፡በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ እነዚህ ሃረጎች እና ቃላቶች የትኞቹ ናቸው?

1. መሳፍንት 2:2____________________________________________
2. መሳፍንት 2:1____________________________________________
3. መሳፍንት 3:7____________________________________________
4. መሳፍንት 8:34___________________________________________

**ትግበራ፡**

እነዚህ ማጠቃለያዎች ማስጠንቀቂያም ይሰጡናል፡፡እነዚህን ማጠቃለያዎች በሙሉ አንድ በአንድ ተመልከቷቸው፡፡ብሉይ ኪዳን ውስጥ ለእስራኤላውያን የተሰጧቸውን መመሪያዎች የሚያለክቱትን ጥቅሶችን በሙሉ ተመልከቷቸው፡፡አያይዛችሁ በአዲስ ኪዳን ለእኛ የተሰጡንን መመሪያዎች ተመልከቷቸው፡፡

| **ማጠቃለያ ሃሳብ** | **ከብሉይ ኪዳን** | **ከአዲስ ኪዳን** |
|---|---|---|
| መታዘዝ | ዘዳግም 6:5-6 | ዮሐንስ 14:15፤23 |
| ማዳመጥ | ዘዳግም 30:20 | ዮሓንስ 10:27-28 |
| አትዘንጉ | ዘዳግም 4:9 | ያዕቆብ 1:25 |
| አስታውሱ | መዝሙር 105:5 | ሉቃስ  22:19 |

1. ለጌታ ያለንን ፍቅር እንዴት ነው የምንገልፅለት?________________________
2. ልንሰማ ብቻ ሳይሆን ______________________________ነው የተጠራነው
3. ከመዘንጋት እንድንጠበቅ ______________________እንድናደርግ እንበረታታለን፡፡

4. ኢየሱስ እንድናስታውሰው ምን አደረገ?______________________________

______________________________________________

ቀጥሎ በተዘረዘሩት ቁጥሮች ውስጥ ቀጣዩን ትውልድ የሚመለከቱ ተግባራዊ መመሪያዎች ተሰጥተውናል ።

- መዝሙር 78፡5-7______________________________
- መዝሙር 145፡4-7______________________________
  - ተናገር______________________________
  - አውራ______________________________
  - አሰላስል______________________________
  - አውጅ______________________________
  - አክብር______________________________

እንዳትረሱ የማስታወስ ብቃታችሁን የምታጠናክሩት ምን አይነት መንገድ እየተጠቀማችሁ ነው?

______________________________________________

______________________________________________

ሰዎች በማይዘነጋ መልኩ ጌታን እንዲያውቁ የምትረዷቸው ምን አይነት መንገድ በመጠቀም ነው?

______________________________________________

______________________________________________

## <u>ትምህርት አምስት-ክፍል 1</u>

**ስለእግዚአብሄር የተማርነው፡**

የምስራቹ ለሁላችንም ነው፡፡

1. በመዝሙር 106፡40-46 ባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር በህዝቡ ላይ ስለተቆጣው ቁጣ ይነግረናል፡፡ነገር ግን ቁጥር 44-46 ያለውን ቀረብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ከአመፃቸው በተቃራኒ ጭንቀታቸውን አሰበ ጩኸታቸውን ሰማ ቃልኪዳኑንም_______________፡፡
2. መዝሙር 111፡5 ቃልኪዳኑን እንደገና _____________________ይነግረናል፣ለአፍታ ሳይሆን______________________________! ከአብርሐም ጋር የገባውን ቃልኪዳን ካሰበ እኛም በልጁ ደም የእርሱ ልጆች የሆንንበትን ይህን እውነት ደግሞ በጥምቀት ቃል የገባንበትን ቃልኪዳን ያስባል፡፡እርሱ አምላካችን ነው እኛም ደግሞ የእርሱ ህዝቦች ነን_____________________ለዘላለም!
3. ኤርሚያስ 31፡33-34 በደላችንን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በኋላ____________ በደላችንን ይረሳዋል!

**ፀሎት፡**

ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፥ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፥ሕይወትሽን ከጥፋት የሚያድናት፥ በምሕረቱና በቸርነቱ የሚከልልሽ፥ ምኞትሽን ከበረከቱ የሚያጠግባት፥ ጎልማስነትሽን እንደ ንስር ያድሳል፡፡እግዚአብሔር ይቅርታ አድራጊ ነው ለተበደሉ ሁሉ ይፈርዳል፡፡ምኞትሽን ከበረከቱ የሚያጠግባት፥ ጎልማስነትሽን እንደ ንስር ያድሳል፡፡" እግዚአብሄር ሆይ በደሌን ስለረሳህልኝ ደግመህ ስለማታስታውሰው አመሰግንሀለሁ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**በጥልቀት መመልከት፡**

የመሳፍንት መፅሐፍ የኢያሱን እንዲሁም እግዚአብሄርን እና ለእነርሱ ያደረገውን ነገር የሚያውቀውን ትውልድ ሞት ተከትሎ በምድሪቱ ላይ ስለተነሱት መሳፍንት ብዙ ታሪኮች በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ተዘግበዋል፡፡ምንም እንኳን እስራኤላውያን ሌሎች አማልክቶችን በማምለክ ማመንዘራቸውን እና መሳፍንቱን መቃወም ባያቆሙም እነዚህ መሳፍንቶች እነርሱን በዙሪያቸው ካሉ ጠላቶቻቸው እንዲታደጓቸው እግዚአብሄር ያስነሳቸው ሰዎች ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ታሪኮች በጣም አስደንጋጭ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ታሪኮች መካከል በመሳፍንት 3 ላይ የተጠቀሰው አንደኛው ምሳሌ ግራኙ ነፃአውጪ ናኦድ ነው፡፡ ሌላው አስከፊ ክስተት የተከናወነው በ መሳፍንት 4 ላይ ዲቦራ በእስራኤል ላይ ፈራጅ ሆና በነበረችበት ወቅት ነው፡፡መሳፍንት ምዕራፍ 6 ጌዲዮን ስለተባለ ጉልህ ሚና ስላለው መስፍን በመተረክ ይጀምራል፡፡ በምዕራፍ 11 የተሳሳተ መሀላ ስላደረገው ዮፍታሄ እናነባለን ፡፡፡እነዚህን ታሪኮች በማንበብ በቅርበት እንድታውቋቸው ትበረታታላችሁ፡፡

**የቤት ስራ፡**

ምናልባት በመሳፍንት መፅሐፍ ውስጥ እጅግ ከታወቁ ገፀባህሪያት አንዱ በድካሙም በብርታቱም የምናውቀው ናዝራዊው ሶምሶን ነው፡፡የሶምሶን ታሪክ መሳፍንት 13 ላይ ይጀምራል፡፡ይህንን ክፍል ስታነቡ የሚከተሉትን ነገሮች ለይታችሁ አውጡ፡፡

- በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ገፀ ባህሪያት፡፡
- ችግሩን
- ስለናዝራዊያን ያለውን እውነታ፡፡
- ከእግዚአብሄር መልአክ ጋር ስላለው ነገር፡፡
- ስለ ተመለሰው ፀሎት

**መልመጃ፡**

- እስራኤልን የተቆጣጠራት ማነው? በቁጥር 1 መሰረት ይህ የሆነው ለምንድነው?

- በታሪኩ ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ የያዘው ማነው?

- የተፈጠረው ችግር ምንድንነበር?

## <u>ትምህርት አምስት-ክፍል 2</u>

**ትምህርት፡**

ናዝራዊ ማለት ምን ማለት ነው?ናዝራዊ "ለእግዚአብሄር የተለየ ሰው" ማለት ነው፡፡የእግዚአብሄር መልአክ ለሴቲቱ ወዲያውኑ ልትፈፅመው እንዲሁም አስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ ልትተገብረው የሚገባትን መመሪያ ሰጣት፡፡እነዚህ መመሪያዎች ምን ነበሩ?

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

- እነዚህ መመሪያዎች የተመሰረቱት በዘኁልቁ 6፡1-21 ባለው ክፍል ነው፡፡በመሳፍንት 13፡3-7 ባለው ክፍል በመልአኩ ስለ ናዝራዊነት የተነገሩትን መመሪያዎች እና ትዕዛዛት አነፃፅሯቸው፡፡

  ______________________________

  ______________________________

  ______________________________

  የናዝራዊው በህዝቡ መካከል መገኘት የእግዚአብሄር ህዝቦች ለቅድስና የተጠሩ እራሳቸውን በዙሪያቸው ካሉ ጣኦታት የለዩ እና በዘላለም ቃልኪዳን የእግዚአብሄር ልጆች የሆኑ አንደሆኑ እንዲያስታውሱ ያደርጋቸዋል ፡፡

**መልመጃ፡**

1. የማኑሄ ፀሎት ምን ነበር? ጥያቄውስ ምን ነበር?

   ______________________________

   ______________________________

2. ማኑሄ እንግዶችን በቤቱ እራት እንዲበሉ ጋበዛቸው፡፡የእግዚአብሄርንም መልአክ ስምህ ማነው አለው?" ምላሹ ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

3. በቁጥር 19-20 ባለው ክፍል ውስጥ የእግዚአብሄር መልአክ እራሱን በምን መልክ ነበር የገለጠው?

______________________________________________

______________________________________________

4. በቁጥር 22-23 መሰረት የማኑሄ እና የሚስቱ ምላሽ ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

5. እግዚአብሄር ለማኑሄ እና ለሚስቱ ቃል የገባላቸውን ሁሉ ፈፀመላቸው፡፡ እግዚአብሔርም ባረከው፡፡ የእግዚአብሔርም መንፈስ____________________እናመካከል ____________________ ሊያነቃቃው ጀመረ፡፡

**ትግበራ፡**

ከዚህ ሁሉ ነገር ተነስተን ይህ ህፃን የተለየ እንደሆነ መናገር እንችላለን፡፡የተፀነሰው መሃን ከሆነች ሴት ነው፡፡ እድሜውን በሙሉ ለእግዚአብሄር የተለየ ሰው ነው፡፡ቤተሰቦቹም እግዚአብሄርን የሚያመልኩ ሰዎች ስለሆኑ ይህን ህፃን እንዴት ማሳደግ እንዳለባቸው መመሪያ እንዲሰጣቸው እና እንዲረዳቸው ወደ እግዚአብሄር ፀለዩ፡፡የተነገራቸውን ነገር በሙሉ አመኑ፡፡

ብዙ ጊዜ ወላጆች በቅድመ ወሊድ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲሁም ልጁ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ደረጃዎችን በማለፍ የልጅነት እድሜ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚረዳቸውን መፃህፍት ያነባሉ፡፡እዚህ በመሳፍንት 13 ላይ ያሉ ወላጆች ግን ያስጨነቃቸው ሌላ ነገር ነበር፡፡እግዚአብሄርን የጠየቁት ይህን ህፃን እግዚአብሄር ለፈለገው አላማ መዋል በሚችልበት ሁኔታ ማሳደግ የምንችልበትን መንገድ አስተምረን ብለው ነበር የፀለዩት፡፡እናንተስ የዚህ አይነት ተመሳሳይ ነገር ቢገጥማችሁ በፀሎት የምትጠይቁት ምን ነበር?______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**መልመጃ፡**

ከዚህ በታች በተጠቀሱት ቁጥሮች ውስጥ የተሰጡት መመሪያዎች ምንድናቸው?

- ዘፍጥረት 18፡19________________________________________
- ዘዳግም 6፡5-9________________________________________
- ምሳሌ 22፡6________________________________________
- ኤፌሶን 6፡4________________________________________

**ትምህርት አምስት-ክፍል 3**

**ትግበራ፡**

ወላጅ የሚሆኑት ሰዎች ብቻቸውን ቢሆኑ፣ከዚህ ቀደም ልጅ የሌላቸው ቢሆኑ ወጣት ወይንም ሽማግሌ ቢሆኑ ማኑሄ የጠየቀውን አይነት ጥያቄ ልንጠይቅ ይገባናል፡፡

1. ለእግዚአብሄር ተለይቻለሁ ስል ለእኔ ምን ማለት ነው?

____________________________________________

____________________________________________

2. ጊዜው እንዳልዘገየ አስቡ እና ቀሪውን የህይወቴን ዘመን ልመራበት የሚገባኝ ምን አይነት መመሪያ ነው የሚያስገፈልገኝ?

____________________________________________

____________________________________________

3. የህይወቴ መሪ ቃል ምንድነው? በአጠቃላይ የህይወቴ አላማ የምኖርለት ነገር ምንድነው?

____________________________________________

____________________________________________

**ፀሎት፡**

ቀጣዩን ህይወታችሁን እንዴት መምራት እንዳለባችሁ እግዚአብሄር እንዲረዳችሁ በፀሎት ጠይቁት፡፡

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

**መግቢያ፡**

በመሳፍንት 13 ማለቂያ ላይ የተወለደው ፍፁም የሆነ፣ወላጆቹን የሚወድ እና የሚያከብር፣በእግዚአብሄር የተባረከ እና የእግዚአብሄር መንፈስ እያነቃቃው ያለ ህፃን አድርገን

እናስባለን። ምዕራፍ 14 ደግሞ ይህ ህፃን አድጎ እና ሙሉ ሰው ሆኖ ያለውን ነገር ይነግረናል።የሶምሶንን ታሪክ እያጠናን ስንሄድ እግዚአብሄር እርሱን የለየበትን አላማ በልባችን እንያዝ።

የመሳፍንት 13:5 መጨረሻ "______________________________ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ __________________________ይሆናልና______________________________እርሱም እስራኤልን ______________________________እጅ ማዳን ይጀምራል።

**የቤት ስራ፡**

መሳፍንት 14 አንብቡ የሚከተከሉትንም ልብ በሉ።

- ሶምሶን የፈለገው ምን ነበር?
- ክርክሩ ምን ነበር?
- በተምናህ መንገድ ላይ ምን ተፈጠረ?
- የሞተውን አንበሳ እና የማሩን ነገር አስቡ።
- በግብዣው ላይ ምን ሆነ ?
- ታሪኩ እንዴት ነው የተጠናቀቀው?

**መልመጃ:**

1. ሶምሶን እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን ነፃ ማውጣት እንደሚጀምር በልባችሁ ያዙ እና ምዕራፍ 14 ሙሉውን አንብባችሁ በጣም ጠቃሚ የሆኑትን የታሪክ እውነታዎች ለይታችሁ አውጡ።

    - ______________________________________________
    - ______________________________________________
    - ______________________________________________
    - ______________________________________________
    - ______________________________________________

ተጨማሪ እውነታዎችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

2. ወጥቶም ለአባቱና ለእናቱ:: በተምና_______________________________ ልጆች አንዲት ሴት አይቻለሁ አሁንም እርስዋን አጋቡኝ አላቸው::ለምንድነው የሶምሶን ወላጆች ይህንን ሃሳብ አጥብቀው የተቃወሙት?

_______________________________________________

3. የእግዚአብሄር መንፈስ በኃይል ወረደበት:: የሶምሶን ጥንካሬ የተገለፀበት የመጀመሪያው ክፍል ነው:: ከሞተው አንበሳ ውስጥ ማር አውጥቶ የመብላቱ ጠቀሜታ ምንድነው? ከዘኁልቁ 6፡6-7 ባለው ክፍል ምን ታስታውሳላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

4. የሳምሶን ሚስት በሙሽርነት ስፍራዋ ወቅት በዙሪያዋ ያሉ ሰዎች ጎተጎቷት::ምን እንድታደርግ ነበር የጎተጎቷት ቁጥር 15?

_______________________________________________

_______________________________________________

5. የሶምሶን ሚስትም ወደቤት ሄዳ በማልቀስ ሶምሶን መቋቋም እስከማይችል ድረስ ነዘነዘችው::የእንቆቅልሹን መልስ ነገራት::ሶምሶን የእንቆቅልሹን መልስ መንገሩ ምንድነበር ያስከተለበት?

_______________________________________________

_______________________________________________

6. ሶምሶን የእንቆቅልሹን መልስ እንዴት እንዳገኙት አውቋል ምክንያቱም መልሱን የነገራት ለእርሷ ብቻ ነበር::ለትክክለኛ ምላሻቸው ምን ነበር ያላቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

7. አሁንም በድጋሚ የእግዚአብሄር መንፈስ በሃይል በእርሱ ላይ መጣበት (ቁጥር 19) :: ምን ነበር ያደረገው?

_______________________________________________

_______________________________________________

ሶምሶን ተቆጥቶ ነበር ፡፡ወዴት ነው የሄደው?________________________________

በሚስቱ ላይስ ምን ሆነ?__________________________________________________

8. ታሪኩን እንዴት እንደሚያልቅ ነው የጠበቃችሁት?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

<u>**ትምህርት አምስት-ክፍል 4**</u>

**ስለእግዚአብሄር የምንማረው፡**

- *በዚህ ምዕራፍ ሶምሶን የተገለፀልን አስቸጋሪ እና ሰው የማያከብር ሆኖ ነው፡፡ የእግዚአብሄርን ህግ እምቢ በማለት እስራኤላዊ ብቻ ማግባት ሲኖርበት እርሱ ግን ለመታዘዝ አልቻለም፡፡በተቃራኒው ፍልስጥኤማዊቱን ሴት ካላገባሁ ብሎ አገባት፡፡ከዛም ቁጥር 4 ላይ እንዲህ የሚል እናነባለን፡ "እግዚአብሔርም በፍልስጥኤማውያን ላይ ምክንያት ይፈልግ ነበርና ነገሩ ከእርሱ ሆነ አባቱና እናቱ ግን አላወቁም፡፡....."ይሄ ሁኔታ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡በርግጥ እግዚአብሄር እንዲህ እንዲሆን ፈልጓል?ይህ ማለት አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሄር ልጆችን ያልሆነ ነገር እንዲጠይቁ እና ሰው አክባሪ እንዳይሆኑ ያደርጋል ማለት ነው?ወይንም እግዚአብሄር አላማውን ለማሳካት አንዳንድ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ማለት ነው?*

  ________________________________________________

  ________________________________________________

- *በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት ጊዜ "የእግዚአብሄር መንፈስ በላዩ ላይ በሃይል ወረደበት የሚል ሃረግ እናገኛለን፡፡ሁለቱንም ጊዜ ሶምሶን ታላቅ የሆነ የሰውነት ጥንካሬ ነው የታየበት፡፡የመጀመሪያው የተጠቀሰው በቁጥር 5-6 ሲሆን ቀጥሎ ያለው ደግሞ በቁጥር 19 ላይ ነው፡፡አንደኛውን ጊዜ __________________________ ሲያደርግ ሲሆን ሁለተኛው ጊዜ ደግሞ __________________________ ሲያደርግ ነው፡፡ሶምሶንን ጥንካሬውን እና ብርታቱን በእርሱ ላይ ሊያሳይ እግዚአብሄር ያስነሳው ሰው ነው፡፡እስቲ እናንተ በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ የእግዚአብሄር ሃይል ሲገለጥ የተመለከታችሁበትን ወቅት አስታውሱ፡፡*
- *ይህ ጥንካሬ ታዲያ የስጋ ጥንካሬ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?የእግዚአብሄር መንፈስ በሃይል ወረደበት የሚለውን ክፍል ስንመለከት ሰለ እግዚአብሄር ምን እንረዳለን?*

  ________________________________________________

  ________________________________________________

**ትምህርት፡**

የእግዚአብሄርን መንፈስ በህይወታችሁ አልተለማመዳችሁ ይሆናል፡፡ሶምሶን በጣም የተለየ ሰው ነበር፡፡ከመሀን ሴት መወለዱ ብቻ አይደለም ልዩ የሚያደርገው ለእግዚአብሄር የተለየ ናዝራዊ መሆኑም ነበር፡፡ እግዚአብሄርን በሚያውቅ እና ይህንን ልጅ እግዚአብሄር ለፈለገው አላማ እንዲውል የሚያሳድጉበትን ጥበብ እንዲሰጣቸው ከሚጠይቁ ቤተሰቦች ነው የተወለደው፡፡

ትደነቁ ይሆናል ፡የእግዚአብሄርን መንፈስ በህይወቴ ካልተለማመድኩ በህይወቴ ውስጥ ችግር አለ ማለት ይሆን? የእግዚአብሄር መንፈስ አንዳች ስሜት አይደለም፡፡በሆነ ስሜት ውስጥ የሚገለጥ ብቻ አይደለም፡፡ፀጥ እና ዝግ ባለ ሁኔታ ውስጥም የእግዚአብሄር መንፈስ ወደ ህይወታችን ይመጣል፡፡ፍቅሩን እና ርህራሄውን ይዞ ወደ ብቸኞች ይመጣል፣የተጎዱትን፣ነገር የተበላሸባቸውን ትኩረት ሰጥቶ ይሰማቸዋል፣ስራዬን አጣለሁ ብለው በፍርሀት ውስጥ ላሉ ፣የስራ እድገት ላመለጣቸው፣በስኬት እና በክንውን ወቅት፣በልደት ወይንም በሰርግ ወቅት እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሄር መንፈስ በኃይል የሚመጣባቸው መንገዶች ምሳሌ ናቸው፡፡

በክርስቶስ በማመን የእርሱ ወደሆኑት የእርሱ መሆናችንን ለማወጅ ስንጠመቅ የእርሱ መሆናችን የዘላለም ህይወትን ማግኘታችንን የእርሱ ልጆች መሆናችንን በሁሉ ፊት እናውጃለን፡፡በደሙ ከኃጢአታችን ነፅተን ልክ የሌለውን ፀጋ እና ምህረት ተቀብለናል፡፡እናንተም ይህን ታላቅ የፀጋውን ስጦታ እና ምህረት ካልተለማመዳችሁ፣የኃጢአታችሁን ይቅርታ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ካልተቀበላችሁ አሁን የእግዚአብሄር መንፈስ በእናንተ ላይ እንዲመጣ እና ያላችሁበትን ሁኔታ እንዲቀይር ፀሎቴ ነው፡፡

**ፀሎት፡**

ኦ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ስለ እኔ ሞተሀል፡፡አንተ አዳኜ ነህ፡፡መንፈስህ በኃይል በእኔ ላይ ይምጣ፡፡የኃይልህን መገለጥ በስሜት አና በሁኔታ ላይ ብቻ ተመስርቼ እንዳልጠብቅ አይኖቼን ከፍተህ መንፈስህ በሁኔታዎች ሁሉ አንተ በእኔ መጠቀም በፈለግክበት ሁኔታ እና መንገድ ስትጠቀምብኝ እና በህይወቴ ውስጥ በሙላት ሲሰራ አሳየኝ፡፡ዛሬ በመልካምነትህ በህይወቴ ስላፈሰስክልኝ በረከቶች ምስጋና እና ውዳሴ ልሰጥሀ እወዳለሁ፡፡

**ክለሳ፡**

በመሳፍንት 13 ላይ ሶምሶን ከመወለዱ አስቀድሞ እንኳን ናዝራዊ እንደሆነ እና ለእግዚአብሄር የተለየ እንደሆነ በቁጥር 5 እንዲሁም እስራኤልን ከፍልስጥኤም ነፃ እንደሚያወጣ ተመልክተናል፡፡(መሳፍንት 14፡2) ላይ ሶምሶን ፍልስጥኤማዊት ሴት ለማግባት እንደመረጠ ተመልክተናል፡፡ይቺን ሴትም እግዚአብሄር ፍልስጥኤማውያንን ነገር ለመፈለግ እንደተጠቀመባት ተመልክተናል (መሳፍንት 14፡4)፡፡ይሁን እንጂ በጣም በመናደዱ ምክንያት ወደአባቱ ቤት ሄደ በዚህም ምክንያት የሶምሶን ሚስት ከሚዜዎቹ ለአንደኛው ተሰጠች፡፡

**ትምህርት አምስት-ክፍል 5**

**የቤት ስራ፡**

መሳፍንት 15 አንብቡ እንደገና የታሪክን እውነታዎች ታገኛላችሁ

- ሶምሶን ወደ ሚስቱ ሲመለስ ምን ገጠመው?
- ሶምሶን የወሰደው የበቀል እርምጃ ምን ነበር?
- የፍልስጥኤማውያን ምላሽ ምን ነበር?
- እስራኤላውያን በዚህ ሁኔታ ውስጥ በምን መልኩ ነበር የተሳተፉት?
- ለሶምሶን ፍላጎት የእግዚአብሄር ምላሽ ምን ነበረ?

**መልመጃ:**

1. ሶምሶን ተመልሶ ወደ ፍልስጥኤማዊቱ ሚስቱ ሲመለስ የገጠመው ነገር ምን ነበር(ቁጥር 1-2)?

   ________________________________________________

2. ለተፈጠረው ችግር የሚስቱ አባት ምላሽ ምን ነበር?

   ________________________________________________

3. ሶምሶን የወሰደው የበቀል እርምጃ ለፍልስጥኤማውያን የሚገባቸውን ፍርድ እንደ ሰጣቸው ተሰምቶት ነበር።ምን ሊያደርግ ነበር ያሰበው (ቁጥር 4-5) ?

   ________________________________________________

   ________________________________________________

4. የፍልስጥኤማውያን ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 6)?

   ________________________________________________

5. የሶምሶን ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 7-8)?

   ________________________________________________

   ________________________________________________

6. የኤጣም ዋሻ የሚገኘው በይሁዳ ነገድ ድንበር ላይ ነው፡፡ሶምሶንን ለመያዝ ፍልስጥኤማውያን በይሁዳ ሰፈሩ፡፡ፍልስጥኤማውያን የፈለጉትን ከተረዱ በኋላ የይሁዳ ሰዎች ያደረጉት ምንደነው (ቁጥር 11-13) ?

______________________________________________

______________________________________________

7. በቁጥር 14 ላይ እንደገና ምን ተፈጠረ?

______________________________________________

8. የሶምሶን በቀል በፍልስጥኤማውያን ላይ የተፈፀመ ይመስላል፡፡ሶምሶን እረክቷል፡፡ያንን ስፍራ ምን ተባለ?

______________________________________________

__________

9. ሶምሶን በእርግጥ የሚያስፈልገው ነገር ነበር (ቁጥር 18 ) ያ ነገር ምን ነበር?

______________________________________________

10. እግዚአብሄር እንዴት ነበር ምላሽ የሰጠው?

______________________________________________

ሶምሶን ብርታት እና ጥንካሬ አገኘ፡፡

11. እስራኤል በፍልስጤም አገዛዝ ስር ነበረች፡፡ሶምሶንም በዚህ ወቅት በእስራኤል ላይ መስፍን ነበር፡፡ለምን ያህል ጊዜ ነበር የገዛው?

______________________________________________

**ትምህርት፡**

ይህ ምዕራፍ የሚያወራው በሙሉ ስለ በቀል ነው፡፡በቀሉ በተናጠል ወይንም በቡድን ነበር የሚካሄደው፡፡በቀል እንደማይጠግብ ረሀብ ነው መቼም አይጠግብም፡፡በቀል የበላይ ለመሆን የሚደረግ ትግል ነው፡፡ብድር የመክፈል ጥረት ነው፡፡አሁን ተመልሼ ወደ አንተ እመጣለሁ ብድሬን ሳልመልስ አልቀርም የሚል ሃሳብ ነው፡፡እኔን የጎዳኸኝን ያክል አንተንም ስትጎዳ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ ቁስሉም አንተ እኔን ካቆሰልከኝ የከፋ መሆን አለበት፡፡እኔን ለጎዳኸኝ ጉዳት

ተመጣጣኝ ነው ይገባሃል ብዬ ያሰብኩትን ሳላደርግ አላርፍም፡፡ይህም አንተ ስህተት እኔ ደግሞ ትክክል እንደሆንኩ ያሳያል፡፡

**የተግዳሮት ጥያቄ፡**

የበቀል መድሃኒት ምንድነው?ከየትስ ይገኛል?

__________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________________________________________

**ትምህርት ስድስት -ክፍል 1**

**ስለእግዚአብሄር የምንማረው፡**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥቅሶች ስለ እግዚአብሄር እና ስለ በቀል ምን ይነግሩናል?

- ዘዳግም 32፡35-

______________________________

______________________________

- ኢሳያስ 2፡12፣17-18-

______________________________

______________________________

- ዘሌዋውያን 19፡18-

______________________________

______________________________

- ሮሜ 12፡17-21-

______________________________

______________________________

የማጠቃለያ ሃሳብ ፃፉ፡፡ከእነዚህ ምንባቦች ስለእግዚአብሄር እና ስለ በቀል ምን እንማራለን?

______________________________

______________________________

______________________________

**ትግበራ፡**

ሆን ተብሎም ሆነ ባለማወቅ ለተደረገብን ክፉ ነገር ስለምንሰጠው ምላሽ ጊዜ ወስደን ማሰብ ይኖርብናል፡፡የተለያዩ በደሎች በየእለቱ ይደርሱብናል፡፡አንዳንዶቹ ነገሮች አግባብነት ያላቸው አይደሉም፡፡አንዳንድ ድርጊቶች እና ምላሾቻችንውም እንዲሁ ደግሞ፡፡ ምላሽ

*የምንሰጠው እንዴት ነው። ሶምሶን በፍልስጥኤማውያን ለደረሰበት በደል ተመጣጣኝ ነው ብሎ ያመነበትን እርምጃ ወስዷል። ፍልስጥኤማውያንም በተመሳሳይ መልኩ ነው ያሰቡት። ከትምህርታችን የተማርነው ነገር ለበቀል እግዚአብሄር ያለውን ምላሽ ነው?*

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

*በእናንተ ላይ የደረሰ ወይንም እናንተ ያደረሳችሁት በደል ወደ አእምሮአችሁ መጥቶ ያውቃል? በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ስንሆን የእግዚአብሄር መመሪያ ምንድነው?*

________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________

*ለደረሰባችሁ በደል እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ የሆነ ምላሽ ለመስጠት የተቸገራችሁት መቼ ነው?*

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

*ጋዜጦች በተለያዩ ምክንያቶች አንዱ በአንዱ ላይ በወሰደው የበቀል እርምጃ የተሞሉ ናቸው።በሚቀጥለው ሳምንት ስለበቀል የሚያወራ ነገር የተፃፈባቸውን ጋዜጦች ፈልጋችሁ አንብቡ ።ከእነዚህ ክፍሎች ምን ተማራችሁ?*

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________

**የምናሰላስለው፡**

*መዝሙር* 94 *አንብቡ ።በቀል የእግዚአብሄር ነው።ዳኛው እግዚአብሄር ነው።እርሱ መጠጊያችን እና የማምለጫ አለታችን ነው ።እርሱ ሮጠን የምንሸሸግበት ነው።ሶምሶን ለመሸሸግ ወደ ኤጣም ዋሻ ሮጠ።እግዚአብሄር አምላካችን በክፉው ቀን ሮጠን የምንሸሸግበት መጠጊያችን ነው።ክፉዎችን ለክፋታቸው ምላሹን ይሰጣቸዋል ያጠፋቸዋልም።ይህ እርሱ ቃል የገባበት ጉዳይ ነው።መዝሙር* 94፡1-2፣22-33 *በካርዳችሁ ላይ ፃፏቸው።አሰላስሏቸው።ካርዱን በእጃችሁ*

ይዛቸችሁ በተለያዩ ወቅቶች ያጋጠሙአችሁን በቀሎች ወይንም እናንተን በቀልን እንድታስቡ ያነሳሱአችሁን ሁኔታዎች ፃፏቸው፡፡

## ትምህርት ስድስት-ክፍል 2

**ትምህርት፡**

በቀልን እግዚአብሄር በሚመልስበት መንገድ መመለስ ከእኛ ተፈጥሮ በላይ ነው፡፡ተፈጥሮአዊ ዝንባሌአችን እራሳችን እንድንበቀል የሚገፋፋ ነው፡፡ኢየሱስ ክርስቶስ በክፉው ፋንታ ክፉውን አለመመለስ ያለውን ታላቅ ዋጋ በማሳየት ምሳሌ ሆኖናል፡፡የሚከተሉትን ቁጥሮች በመመልከት እነዚህ ክፍሎች የሚያሳዩንን እውነታ ተመልከቱ፡፡

| ጥቅሶች | ትምህርት |
|---|---|
| ማቴዎስ 5፡44-45 | |
| ሉቃስ 23፡34 | |
| የሐዋሪያት ሥራ 7፡59-60 | |
| ሮሜ 12፡14-21 | |
| 1ጴጥሮስ 2፡23-24 | |
| 1ጴጥሮስ 3፡9 | |

ክፉ ሲደረግብን ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንዳለብን ከላይ የተፃፉትን ክፍሎች የሚያስተምሩንን እውነት ማጠቃለያ ፃፉ፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

**ፀሎት፡**

ጌታ ሆይ እራሴን በሌሎች ተበድዬ አግኝቼዋለሁ፡፡አንተም በመስቀል ላይ በተሰቀልክ ጊዜ ይህን አይነት ስሜት ተሰምቶሃል፡፡ይህን የሚያክል ቅጣት ያውም ሞት እንድትቀጣ የሚያደርግህ ምን አይነት ጥፋት ተገኝቶብህ ነው? ዝም ነበር ያልከው፡፡ የበቀል ፍላጎት አልነበረህም፡፡አባትህንም በክፉው ፋንታ ክፉ እንዲመልስባቸው አልጠየቅኸውም፡፡ነገር ግን

ስለእኔ ዝም አልክ፡፡እባክህ ይህን የማደግርበት ኃይል ስጠኝ፡፡በሌሎች ላይ በቀልን ከማሰብ ይልቅ አንተ እኔን እንደወደድከኝ እንድወዳቸው አድርገኝ፡፡

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**መግቢያ፡**

መሳፍንት 16፡1-22 ጀምሮ የሚጨርሰው በፍልስጥኤም ድንበር ደቡባዊ ክፍል በምትገኘው በጋዛ ከተማ ነው፡፡ይቺን ከተማ በካርታችሁ ላይ በሜዲትራኒያን ባህር ዳርቻ ከሙት ባህር በስተ ምዕራብ አመልክቱ፡፡የሶምሶን እና የደሊላ ታሪክ ሶምሶን ለኃጢአት ያለውን ዝንባሌ የሚገልፅ ታሪክ ነው፡፡ለማኑሄ እና ለእናቱ እግዚአብሄር ልጃቸው ሶምሶን ናዝራዊ እንደሆነ ነግሯቸዋል፡፡ሶምሶንን ልዩ ከሚያደርጉት ማንነቶች አንዱ ፀጉሩ ተቆርጦ አለማወቁ ነው መሳፍንት 13፡5፡፡

ሌላው ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ እውነታ ሶምሶን እንደናዝራዊ እስራኤልን ከፍልስጥኤም አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የተለየ መሆኑን ነው፡፡አሁንም በድጋሚ እስራኤል ከፍልስጥኤም እጅ ነፃ ያወጣቸውን አምላክ እግዚአብሄር ላይ ክፉ አደረጉ፡፡መሳፍንት 13፡1፡፡ፍልስጥኤማውያን ብረትን ቀድመው መጠቀም ስለጀመሩ ኃይለኛ እና የማይደፈሩ ህዝቦች ናቸው፡፡በአብዛኛው የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ፍልስጥኤማውያን የእስራኤላውያን ጠላቶች ሆነው ነው የምናገኛቸው፡፡እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ሲወርሱ ምድሪቱ ላይ የቀሩ ቅሬታዎች ናቸው፡፡በሶምሶን አገዛዝ ዘመንም የእስራኤል ፈተናዎች መሆናቸውን ቀጥለው ነበር፡፡

የሶምሶን እና የደሊላ ግንኙነት  ሁላችንም የምናውቀው ነው፡፡ሆሊውድ የተባለው የአሜሪካ የፊልም ድርጅት ይህንን ታሪክ በፊልም ሰርቶታል ነገር ግን ይህንን ፊልም የሚመለከቱ ብዙዎች ሶምሶንን እግዚአብሄር ቅዱስ ለሆነው አላማው የለየው ሰው እንደሆነ አይረዱም፡፡በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ተመልከቱ  ከዚያም ይህ ታሪክ በእርግጥ የፍቅር ታሪክ መሆን አለመሆኑን መርምሩ፡፡

**የቤት ስራ፡**

መሳፍንት 16፡1-22 አንብቡ፡እነዚህን የታሪክ እውነታዎች ተመልከቱ፡፡

- በዚህ ታሪክ ውስጥ ገፀ ባህሪው ማነው?
- እቅዱ ምን ነበር ?
- ታሪኩ የሚደመደመው እንዴት ነው?

**ትምህርት ሶስት-ክፍል 3**

**መልመጃ፡**

1. የጋዛ ህዝቦች ፍልስጥኤማውያን ምን ለማከናወን አቀዱ ቁጥር 1-2 ?

   ______________________________

   ሀ. ሶምሶን የት ነው ያለው?

   ______________________________

   ለ. እንዴት አመለጠ ቁጥር 3 ?

   ______________________________

2. አሁን ደግሞ ደሊላ የሶምሶን ህይወት አዲስ ፍቅረኛ ሆናለች (ቁጥር 4)። ቀን እና ሌሊት መላ እና ዘዴ ትፈልጋለች ።ለመሆኑ ደሊላ ከፍልስጥኤማውያን ባለስልጣናት ጋር ያደረገችው ስምምነት ምንድነው ?

   ሀ. ምን ልታደርግ ነው?

   ______________________________

   ለ. ለዚህ ስራ የሚከፈላት ምን ነበር?

   ______________________________

   ______________________________

3. ደሊላ ሶምሶንን ሶስት ጊዜ የኃይሉ ሚስጥር ምን እንደሆነ ጠየቀችው እሱም ሶስት ጊዜ ዋሻት።አሁን የስልቷን መጨመር ልብ በሉ፡

   ሀ.ቁጥር 6፡______________________________

   ለ.ቁጥር 10፡______________________________

   ሐ.ቁጥር 13፡______________________________

   ደሊላ ለግል ጥቅሟ ሟች ናት።

4. ሶስት ጊዜ ያክል ሶምሶን አሳሳች እና የማታለል ምላሽ መለሰላት፡

   ሀ. ቁጥር 7፡______________________________

   ለ. ቁጥር 11፡______________________________

   ሐ. ቁጥር 13፡______________________________

ሶምሶን የኃይሉን እና የጥንካሬውን ሚስጥር ከደሊላ በመደበቁ ይደሰት ነበር፡፡

5. የደሊላ ክስ ምን ነበር (ቁጥር 10፣13፣15) ?

______________________________

______________________________

6. ደሊላ የሶምሶንን የብርታቱን ሚስጥር አገኘች ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል (ቁጥር 16)?

______________________________

7. በብዙ ንዝነዛ እና ጭቅጨቃ ሶምሶን ሁሉንም ነገር ነገራት፡፡ደሊላም ተሳካላት፡፡ የምትፈልገውንም መረጃ አገኘች ክፍያውን ይዘው ለሚጠብቋት ፍልስጥኤማውያን ባለስልጣናት ነገረቻቸው ፡፡ ተኝቶ ሳለም ፀጉሩን ቆረጠችው ከዚያም______________ ______________________________ (ቁጥር 19)

8. ሶምሶን ከእንቅልፉ ሲነቃ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 20) ?

______________________________

______________________________

ሀ. ፍልስጥኤማውያን ያዙት፡፡ይዘውስ ምን አደረጉበት?

______________________________

ለ. ወዴት ወሰዱት?

______________________________

ሐ. ምን እንዲሰራ አደረጉት?

______________________________

የተስፋ ጭላንጭል ያለበት የሚመስለው ቁጥር 22 ምን ይላል?

______________________________

______________________________

**ገለፃ፡**

አንድ ሰው ይህንን ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል፡ እየሆነ ያለው ነገር ምንድነው? መለኮታዊ የስጋ ብርታት የተሰጠው ፣ሲወለድ ጀምሮ ለእግዚአብሄር የተለየ ሰው፣እስራኤልን ለሃያ

አመታት የመራ ሰው ፣ እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን ጭቆና ነፃ ማውጣት የጀመረ ሰው እነሆ ፡፡ያው ሰው አሁን ደካማ ነው፣ዓይኑ ጠፍቷል፣በእስር ቤት ውስጥ ዱቄት እየፈጨ ይገኛል፡፡እንዲያጠፉቸው የተላከባቸው ጠላቶቹ አሁን እሱን አጠፉት፡፡

ያልተገራው የሶምሶን ያታዊ ፍላጎት ዛሬ ለጥፋቱ ምክንያት ሆነበት፡፡ ወላጆቹን ፍልስጥኤማዊቱን ሴት እንዲያጋቡት አስገደዳቸው (መሳፍንት 14:2)፡፡ በማመንዘሩ ምክንያት ከእንግዳ ሴት ጋር በፍቅር ወደቀ (መሳፍንት 16:4)፡፡እያንዳንዱን ግንኙቱ ያስከተለው የመረረ ውጤት ነበረ፡፡ከመጀመሪያ ሚስቱ ጋር የነበረው ሁኔታ በእንቆቅልሽ የተመሰረተ ሲሆን ያስከፈለው ደግሞ የሰላሳ ሰዎች ልብስ ነው፡፡ ከጋዛ ህዝቦች ጋር በማመንዘሩ ሊገድሉት በሞከሩ ጊዜ የከተማይቱ በር ተሰበረ፡፡በደሊላ ምክንያት ደግሞ ከእግዚአብሄር የተሰጠው ጥንካሬ እንዲሁም እራሱ እግዚአብሄር ተወው፡፡ ይህ ሰው ስለተጓዘው የሞኝነት ጉዞ ከዚህ ውጪ ምን ሊከፈለው ይገባል?

የሶምሶንን ህይወት ስንቃኝ ልክ የሙሉ ሰው ቁመና እና ጥናካሬ ያለው ነገር ግን ብስለት እና ስርአት የጎደለው የህፃን ባህሪይ ያለው ሰው ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ስሜቱ ወደነዳው የሚጓዝ ሰው ነበር፡፡ባህሪው ጥንካሬ ያለው አይደለም፡፡በውጤቱም ለራሱ ያልተገራ ስሜት ሰለባ ሆነ ፡፡ በፊቱ የቀረቡትን ፈተናዎች በጥበብ መመርመር እና መለየት አልቻለም ነበር፡፡

ቀኑን ሙሉ በእስር ቤት ውስጥ በሰንሰለት ታስሮ ዱቄት ሲፈጪ መዋል ሲታሰብ እጅግ የሚያስገርም ነገር ነው፡፡እስቲ እንዲህ አስቡ አንድ ማለዳ ሶምሶንን ዱቄት በሚፈጭበት ስፍራ ሄዳችሁ ቃለመጠይቅ አደረጋችሁለት እንበል ፣ልትጠይቁት የምትችሉት ሶስት ጥያቄዎች ምንድናቸው? የጥያቄዎቻችሁ መልሶች የአዎን እና የአይደለም መሆን የለባቸውም፡፡ ጥያቄዎቻችሁም “ለምን” ? በሚል ቃል መጀመረር የለባቸውም፡፡

- ____________________________________________
- ____________________________________________
- ____________________________________________

## ትምህርት ስድስት-ክፍል 4

**ትግበራ፡**

የራሳችንን ህይወት ጥንቃቄ መመርመር ካልቻልን የሶምሶን ህይወት በጥንቃቄ ልንመረምር አንችልም፡፡ እስቲ ጊዜ ወስዳችሁ የተሳሳተ የውሳኔ አቅጣጫ እንድትይዙ የሚያደርጉአችሁን እና ክፉ ነገር እንድታደርጉ የሚገፋፉችሁን ሁኔታዎች አስቡ፡፡

__________________________________________________________________

እነዚህ ነገሮች ምን እያሉ ሲሸነግሉአችሁ ሰማችኋቸው?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

ስለ ውሸት እና ስለሞኝነት በምን መልኩ ከሰሱአችሁ?

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

የፈተናዎችን ጫና ለመቋቋም እንድትወስኑ የሚያበረታችሁ ምንድነው?

__________________________________________________________________

**መልመጃ:**

በራሳችን ጥንካሬ ላይ የምንደገፍ ከሆነ እግዚአብሄር ያዘጋጀልንን ጥንካሬ መቀበል አንችልም፡፡ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቁጥሮች ስለእውነተኛው ጥንካሬ ምን ያስተምሩናል?

| ጥቅሶች | ትምህርት |
|---|---|
| ዘፀአት 15፡2 | |
| 2 ሳሙኤል 22፡33 | |
| መዝሙር 46፡1 | |
| ኢሳያስ 40፡31 | |
| 1 ቆሮንጦስ 1፡25 | |
| 1 ጴጥሮስ 4፡11 | |

**ማሰላሰል፡**

ፊልጵስዮስ 4፡13 የምናሰላስለው አጭር ክፍል ነገር ግን ድንቅ እውነትን የያዘ ክፍል ነው፡፡ይህ ክፍል የማይቻል የሚመስለውን ማንኛውንም ነገር እንኳን ማድረግ እንደምንችል ያስታውሰናል፡፡ "ሁሉን" የሚለው ቃል ማንኛውንም ነገር ያመለክታል፡፡ የጥንካሬዎች ሁሉ ምንጭ ጌታ ነው፡፡ሁሉን ነገር በእርሱ ማድረግ እችላለሁ፡፡ብርታት እና ጥንካሬን የሚሰጠን ፣የሚያበረታኝ እሱ ነው፡፡ አሁንም ይህንን ክፍል በካርዳችሁ ላይ እንድትፅፉት ትበረታታላችሁ፡፡ እያሰላሰላችሁት ተደሰቱበት ፡፡ ለስጋዊም ፣ለአእምሮአዊም፣ለስሜታዊም፣ሆነ ለመንፈሳዊ ጥንካሬያችሁ የብርታት ሁሉ ምንጭ በሆነው ጌታ ላይ ተጣበቁ ፡፡

**ፀሎት፡**

ኤፌሶን 3፡16 እና ቆላስያስ 1፡11 ላይ ተመርኩዛችሁ ፀሎታችሁን ፃፉት፡፡በእነዚህ ክፍሎች ላይ የተፃፉትን (ተውላጠ ስሞችን) ስም አመልካቾችን በራሳችሁ ስም በመተካት ይህንን ፀሎት የግላችሁ አድርጉት፡፡ወላጆች በእነርሱ መመሪያ መሰረት ልጆቻቸው ሲናገሩ ደስ እንደሚላቸው እግዚአብሄርም በቃሉ ወይንም በመመሪያው መሰረት ስናናግረው ደስ ይሰኛል፡፡

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

**የቤት ስራ፡**

ሶምሶን ተይዟል፤ዓይኑ ወጥቷል ፣ፍልስጥኤማውያን በጋዛ እስር ቤት ውስጥ ዱቄት እያስፈጩት ነው፡፡መሳፍንት 16፡22 ፀጉሩ እንደገና ማደግ ጀመረ ይለናል፡፡ጥንካሬውም እየተመለሰ መጣ፡፡መሳፍንት 16፡23 በማንበብ የሚከተሉትን ነገሮች ተመልከቷቸው፡፡

- ፍልስጥኤማውያን ደስታቸውን የገለፁት ለምንድነው?
- ይዝናኑ የነበረው በምንድነው?
- የሶምሶን ፀሎት ምን ነበር?
- እግዚአብሄር የሶምሶንን ፀሎት እንዴት ነበር የመለሰው?

**መልመጃ፡**

1. የፍልስጥኤም ገዢዎች ምን ለማድረግ ነው የወሰኑት (ቁጥር 23) ?

2. ለሶምሶን መያዝ ክብሩን የሰጡት ለማነው?

3. በቀላቸውን ፈፀሙ።ሳምሶንን በጠላትነት ሊመለከቱት የቻሉት ለምንድነው ቁጥር 24? ይህን ክፍል ተመልሳችሁ ተመልከቱት፡
   ሀ. መሳፍንት 14፡19-
   ለ. መሳፍንት 15፡3-5-
   ሐ. መሳፍንት 15፡14-15-
4. ህዝቡ ተሰብስቦ እየበላ እና እየጠጣ ሶምሶን ተጠራ።ምን እንዲያደርግ ነበር የፈለጉት (ቁጥር 25)?

5. ሶምሶን አገልጋዩን ምን እንዲያደርግለት ለመነው ቁጥር 26?

6. በቁጥር 27 ላይ ስለ ዳጎን ቤተመቅደስ ምን እንማራለን? ሶምሶንን ለማየት የተሰበሰቡት እነ ማን ናቸው?

7. የሶምሶን ፀሎት ምን ነበር?

8. ሶምሶን እጆቹን በሁለቱ የቤተመቅደሱ ዋና ምሰሶዎች ላይ አደረገ።የመጨረሻ ቃሉ ምን ነበር?

   ሀ. በሙሉ ኃይሉ ምሰሶዎችን ገፋቸው ከዚያም

   ለ. ከእነርሱ ጋር አብሮ የሞተው ማነው?

9. በቁጥር 31 ላይ ምንድነው የተነገረን?

**<u>ትምህርት ስድስት-ክፍል 5</u>**

**ገለፃ፡**

ፍልስጥኤማውያን ትልቁን በቀል የተበቀሉት እነርሱ እንደሆኑ አስበዋል፡፡አምላካቸው ዳጎን ሶምሶንን አሳልፎ ስለሰጣቸው መስዋእት እና የፈንጠዝያ በአል አዘጋጅተዋል፡፡ነገር ግን ሶምሶን በዚህ በመጨረሻ ሰአት ሊበቀላቸው እያሰበ ነው፡፡ ቁጥር 28 ላይ ሁሉን የሚችለውን አምላክ ስለጠፉት አይኖቹ እንዲበቀል አንድ ጊዜ እንዲያስበው እየተማፀነ ነው፡፡ በሚታየው ስጋዊ ማንነቱ የስጋው አይኖች ጠፍተዋል፡፡ምናልባት መንፈሳዊ እይታውም ጠፍቶ ይሆን? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ህዝቡ ሶምሶን ተላልፎ በእጃቸው ስለተሰጣቸው በመብላት እና በመጠጣት ደስታቸውን በአምላካቸው ዳጎን ፊት የሚገልጡበት በአል ላይ እየተደሰቱ ነው፡፡ድሉን የሰጣቸው አምላካቸው ዳጎን እንደሆነ አስበው ለእርሱ ብዙ መስዋእት ያቀርቡለት ነበር፡፡ሶምሶንን እግዚአብሄር አንድ ጊዜ እንዲያስበው እና ጥንካሬውን እንዲመልስለት እንዲጠይቀው ያደረገው እነዚህ ሰዎች ይህን የውሸት አምላክ ስላመለኩ ቀንቶ አይለም፡፡ነገር ግን ፍልስጥኤማውያን ሁለቱንም አይኖቹን ስላሳጡት ስለሁለቱ አይኖቹ መበቀል ፈልጎ ነበር እግዚአብሄርን የጠቀየቀው፡፡

- ሶምሶንን ይህን አይነት አመለካከት እንዲኖረው ያደረገው ምንድነው? ለምን ይሆን እግዚአብሄር እርሱን ለቅዱስ አላማው የለየው እንደነበር የዘነጋው?

  __________________________________________________________

  __________________________________________________________

- የሶምሶን ፍልስጥኤማውያንን መበቀል እንዴት አድርጎ ነገሮችን ከእግዚአብሄር አንፃር መመልከት የሚችልበትን ሁኔታ ሊተካለት ይችላል?

  __________________________________________________________

  __________________________________________________________

- ሶምሶን ፍልስጥኤማውያን በዳጎን ቤተመቅደስ ውስጥ እያደረጉት ያሉትን ነገሮች አጥርቶ ተመልክቶ ይሆን እግዚአብሄር እንዲበቀልለት የፈለገው? እስቲ የራሳችሁን መልስ ስጡ፡፡

በመሳፍንት 16፡23-31 ያለውን የሶምሶንን አሳዛኝ ፍፃሜ በተመለከተ ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ በማንበብ ሃሳባችሁን በፅሁፍ ግለፁ፡፡

**ፀሎት፡**

ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ በቀል በሶምሶን ህይወት ውስጥ ያስከተለውን ጥፋት ተመልክተናል፡፡በህይወት ላይ የሚያስከትለውን ታላቅ የሞት ጥፋት ተመልክተናል፡፡ሶምሶን ጤናማ የሆውን አመለካከቱን በማጣቱ ምክንያት ፍፃሜው ሞት እንደሆነ ተመልክተናል፡፡እባክህ በህይወቴ ውስጥ ያለውን አጥፊ የሆነውን ጥላቻ በማስወገድ ፍቅርህን እና ይቅርታህን በህይወቴ ሙላልኝ፡፡ አይኖቼ ሁልጊዜ የበጎ እና ፍፁም ስጦታ ምንጭ የሆንከውን አንተ ላይ ብቻ ያተኩሩ፡፡ህይወቴን በርህራሄ ሙላው በፀጋህ እና በምህረትህ አስታጥቀኝ በክፉው ፋንታ ክፉ የምመልስ ሳይሆን በክፉው ፋንታ መልካም እንድመልስ አድርገኝ፡፡

**የመሳፍንት መፅሐፍ እንዲህ በማለት ያጠቃልላል፡**

የቀሩትን የመሳፍንት መፅሀፍ ምዕራፎች በሙሉ በዝርዝር አንመለከታቸውም፡፡በጣም ብዙ ጊዜ የተደጋገመ አንድ አረፍተ ነገር አለ፡፡ በመሳፍንት 17፡6፣18፡1፣19፡1 እና 21፡25 ላይ የተነገረን ምንድነው ?

አለመታመን ተስፋፍቷል ከሁሉ በላይ ግን ጣኦት እና የተለያዩ ምስሎች ተሰርተዋል ፣ተመልከዋል በእስራኤላውያን ቤቶችም ተቀምጠዋል፡፡ክህናቱም ግራ ተጋብተዋል የእግዚአብሄርን ሳይሆን የራሳቸውን ነገር ነው የሚፈልጉት፡፡በወቅቱ የነበረውን የህይወት ስርአት እንዲህ በሚል አረፍተ ነገር ተደጋግሞ ተገልጧል፡ “በዚያንም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉስ አልነበረም ሁሉም በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር፡፡” የመሳፍንት መፅሐፍ በእነዚህ ቃላት ነው የሚደመደመው፡፡

የእግዚአብሄርን ህጎች እና ትእዛዛት በመተው እስራኤላውያን የራሳቸውን ህግ አውጥተዋል፡፡ እራሳቸውን ህይወታቸውን የሚቆጣጠሩ አማልክት አድርገዋል፡፡ህጋቸው “ህግ የለም” የሚል ነው፡፡ ለእግዚአብሄር የተለዩ የሆኑበትን መታወቂያ አጥተዋል፡፡ እንደ አንድ ህዝብ እንዲኖሩ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በመዘንጋት ለግል ጥቅማቸው በተናጠል መኖርን መርጠዋል፡፡

“ሁሉም በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር” የሚለውን ቃል ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይህን አይነት አካሄድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ለውጥ እንደሚያመጣ ታስባላችሁ፡

- በማህበረሰብ ውስጥ ?

  ______________________________

- በቤተሰብ ውስጥ ?

  ______________________________

- በራሳችሁ ህይወት ላይ ?

  ______________________________

**ክለሳ**

ከባለፈው ጥናታችሁ በመነሳት ስማቸውን የምታስታውሷቸውን ሰዎች ለዩ፡፡የእነዚህን ሰዎች ማንነት ይገልፃል ብላችሁ የምታስቡትን ጥቂጥ ነገር ፃፉ፡፡ ሁሉንም ማስታወስ ካልቻላችሁ እንዳትጨነቁ፡፡ ይህ ፈተና ሳይሆን የማስታወስ አቅማችሁን ለማሳደግ የታቀደ ጥያቄ ነው፡፡

| ስም | ስለእነርሱ የምታስታውሱት | የሚገኝበት ክፍል |
|---|---|---|
| ኢያሱ | | ኢያሱ 1 |
| ረአብ | | ኢያሱ 2 |
| አካን | | ኢያሱ 7 |
| ናኦድ፣ዲቦራ፣እና ጌዲዮን | | ኢያሱ 3-6 |
| ናዝራዊ | | ኢያሱ 13፡7 |
| ሶምሶን | | ኢያሱ 13 |
| ፍልስጥኤማውያን | | ኢያሱ 13፡1 |
| ደሊላ | | ኢያሱ 16 |

ጥቂት ሃረጎች እና ቃላቶች በጥናቶቻችን ተደጋግመው ተጠቅሰዋል፡ እስቲ የምታስታውሷቸውን ጥቂቶቹን ፃፉ፡፡ ከየት መጀመር እንዳለባችሁ እንዲረዳችሁ ጥቂቶቹ ተገልፀዋል፡፡

1. ኢያሱ 1፡6________________________________________
2. ኢያሱ 10፡28______________________________________
3. ኢያሱ 11፡23______________________________________
4. መሳፍንት 1፡19____________________________________
5. መሳፍንት 2፡11____________________________________
6. መሳፍንት 14፡19___________________________________

ምድራቸውን ፣ አመራራቸውን፣ ምድሪቱን መውረሳቸውን ፣ያለ ንጉስ መኖራቸውን ፣ የመንፈሳዊ ህይወታቸውን መውጣት እና መውረድ  እንዲሁም ከእግዚአብሄር ውጪ ሌሎች አማልክቶችን ማምለካቸውን በተመለከተ በኢያሱ እና በመሳፍንት መፃህፍት በእስራኤላውያን ላይ ምን እንደደረሰባቸው በሶስት ወይንም በአራት ዓረፍተ ነገሮች ግለፁ፡፡

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________